አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የመምህር መምሪያ



## ፩ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

## ፩(1)ኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


**አዘጋጆች**

መዓዛ ታረቀኝ ወርቅነህ

እሸቱ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ

ዩሱፍ ማሩ ፈረጅ

**ገምጋሚና አርታኢዎች**

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

**የጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ**

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

**አስተባባሪ**

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

**አቀማመጥ እና ስዕል**

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

© መብቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተጠበቀ ነው፡፡
2014 ዓ.ም አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለሥራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ ገጽ

መግቢያ........................................................................................IV

1. ምዕራፍ አንድ ...............................................................1

ቤተሰብ

2. ምዕራፍ ሁለት.....................................................................11

ቤት

3. ምዕራፍ ሦስት ...............................................................20

ትምህርት ቤት

4. ምዕራፍ አራት.....................................................................29

ጓደኞቼ

5. ምዕራፍ አምስት..................................................................39

ተክሎች

6. ምዕራፍ ስድስት...................................................................49

የመንገድ ደህንነት

7. ምዕራፍ ሰባት ..................................................................58

ተረት

8. ምዕራፍ ስምንት .............................................................68

ምግብ

9. ምዕራፍ ዘጠኝ......................................................................77

የግል ንፅህና አጠባበቅ

10. ምዕራፍ አስር ..................................................................87

የቤት እንስሳት

መርኃ ትምህርት.........................................................................................95

ዋቢ መፅሐፍት.........................................................................................

አባሪዎች

# • መግቢያ

## ለተጠቃሚዎች

ይህ መጽሐፍ የ1ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ በእኩል ደረጃ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

## መርህ አንድ

ተማሪዎች ስዕሎችንና ርዕሶችን በመመልከት የቅድመ ማዳመጥና ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲገምቱ በማድረግ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥና በማንበብ የማዳመጥና የማንበብ፣ የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

## መርህ ሁለት

ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንም ንባብ በሚገባ በማዳመጥና በማንበብ የአዳምጦ/የአንብቦ መረዳት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

## መርህ ሶስት

ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንደየአጠያየቃቸው የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያለማምዷቸው፡፡

## መርህ አራት

ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ልልምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው፡፡

## መርህ አምስት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቻቸውን አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

# ለመምህራን

ውድ መምህር ተማሪዎች የቋንቋን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባትተማሪዎችን በሚገባ ሊያግዟቸው ይገባል ፡፡

፩ ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን… ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው፡፡/

፪. ለተማሪዎች የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ተማሪዎች መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ እንዲሁም የራሳቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

፫. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን እንደየመመሪያቸው በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

፬. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

፭. ለተማሪዎች በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የተለያዩ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ አንድ
# ቤተሰብ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ስለጽህፈት ጽንሰ ሃሳብ የቀረበውን ገለጻ ያዳምጡና ከጓደኞቻቸው ጋር ይወያያሉ፤
- ተዘውታሪ ቃላትን ይዘረዝራሉ፤
- አዳዲስ ሆሄያትን/ድምፆችን ይለያሉ፤
- በፊደል ገበታ ላይ ያሉትን ሆሄያት ሁሉ በትክክል ይቀርጻሉ፤
- ተገቢ የሆነ የእርሳስና እስክሪፕቶ አያያዝን ይማራሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## ማዳመጥ

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ታሪክ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ትኩረታቸው ከርስዎ ጋር መሆኑን ለማረጋገጥ ምንባቡን በመሃል ቆም በማድረግ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ምላሻቸውን እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ታሪኮችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

# ቤተሰብ

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ስድስት አባላት ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ እናት፣ አባት ወንድም ፣እህት አያት ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡ በእድሜ ትልቆቹ አያቶች ሲሆኑ ከዚያም የሚቀጥሉት እናትና አባት ናቸው፡፡ ትንሾቹ ደግሞ ልጆች ናቸው፡፡

## አዳምጦ መናገር

*መምህር፡-*

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- (ሀሳባቸውን ይቀበሏቸው)

## ተዘውታሪ ቃላት

*መምህር፡-*

- ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተዘውታሪ ስሞችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡በቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ ስሞችን ከስዕላቸው ጋር እያዛመዱ (እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣....) ለይተው እንዲናገሩ ያበረታተቷቸው፡፡
- ስዕሎችን እያዩ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- እየደጋገሙ እንዲያሳዩ እድል ይስጧቸው፡፡

## ☞ ተተኳሪ ቃላት

*መምህር፡-*

- ተማሪዎች ከትምህርት መሳሪያዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቁሳቁሶች ለይተው እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡
- ከመፅሐፍ ጋር የተያያዙ የተለመዱ ቃላትን (ርዕስ፣ የመፅሐፍ የፊት ሽፋን፣ የኋላ ሽፋን፣ …) ከመፅፋቸው የቀረበውን ስዕል በማየት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የእርሳስ አያያዝ፣ የእስክርቢቶ አያያዝ፣ የመፅሐፍ አያያዝ እንዴት እንደሆነ ከላይ ወደታች፣ ከግራ ወደ ቀኝ ያሳዩዋቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

*መምህር፡-*

- ተማሪዎች ከቤተሰብ ስም ጋር የተገናኙ ስሞችን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- የቤተሰብ የዘር ሃረግ የሚያሳይ የዛፍ ሞዴል ወይም የሃሳብ ካርታ በቅድሚያ ያዘጋጁ፡፡
- የቤተሰብ የዘር ሃረግ ያለበትን የዛፍ ሞዴል ወይም የሀሳብ ካርታ ለተማሪዎች በግልፅ በሚታይ ቦታ ይለጥፉት ወይም ያንጠልጥሉት፡፡
- ተማሪዎች የዘር ሃረጎችን በሐሳብ ካርታ ላይ እንዲሞሉ ያድርጉ፡፡
- የሀሳብ ካርታው በጅምር የተተዎ ሆኖ ቀሪዎችን ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ገልብጠው እንዲሞሉት ያስደርጉ፡፡
- እየተዘዋወሩ ተማሪዎች እንዴት መፃፍ እንዳለባቸውና የእርሳስ አያያዛቸው ምን መምሰል እንዳለበት በሚገባ ያሳዩዋቸው፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

## ትዕዛዝ፡- የቤተሰብ አባላትን ጻፉ፡፡



## ☞ የፅሕፈት ጽንሰ ሀሳብ

### መምህር፡-

- ተማሪዎች ፊደላትን ለመቅረፅ የሚያገለግሉ መሰረታዊ የፅሕፈት እሳቤዎችን በጥቁር ሰሌዳ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣... ላይ ቀርፀው ያሳዩዋቸው፡፡
- ቋሚ መስመር፣ አግድም መስመር፣ ስላች፣ ግራ ቅንፍ ፣ ቀኝ ቅንፍ እና ቀለበትን በነጠብጣብና በመስመር ቀርፀው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች የፅሕፈት እሳቤዎችን በደብተራቸው ከመቅረፃቸው በፊት የመስመሮቹን አቀማመጥ ያስታውሷቸው፡፡
- ተማሪዎች የፅሕፈት እሳቤዎችን ለመቅረፅ ደብተርና እርሳስ መያዛቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የፅሕፈት እሳቤዎችን በደብተራቸው እንዲቀርፁ ያድረጉ፡፡
- ተማሪዎች የፅሕፈት እሳቤዎችን ሲቀርፁ የእርሳስ አያያዛቸውን እየተዘዋወሩ ይመልከቱ፡፡
- ደጋግመው እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በትክክል መቅረፃቸውን በመከታተል ድጋፍ ያድርጉ፡፡

## ☞ የተተኳሪ ፊደልን ቅርፅ መለየት

### መምህር፡-

- ተማሪዎች የፊደላትን ቅርፅ በጥቁር ሰሌዳ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በፊደል ካርድ፣ በስዕሎች፣ በቅርፃቅርፅ፣ በካርቶን ላይ በመቅረፅ ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች የፊደላቱን ቅርፅ ከእግራቸው አኳያ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

## የተተኳሪ ፊደልን ቅርፅ መለየት

1. ባለ አንድ እግር ፊደል
   ቀ ተ ቸ ነ ኘ የ ገ ፐ ኀ
2. ባለ ሁለት እግር ፊደል
   ለ ሰ ሸ በ አ ኸ ዘ ዠ ደ ጸ ጀ ጰ ቨ
3. ባለ ሶስት እግር ፊደል
   ጠ ጨ ሐ
4. እግር አልባ ፊደል
   ሠ መ ወ ዐ ፀ ሀ ፈ ረ

## ✍ጽሕፈት

### መምህር፡-

- ተማሪዎች የፊደላቱን ቅርፅ የባለአንድ እግር፣ የባለሁለት እግር፣ የባለሶስት እግር እና እግር አልባ የሚባሉትን ሆሄያት ደጋግመው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- እገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎች ካሉ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡-

- የዕለቱን ትምህርት አላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ስዕሎቹን እንዲገምቱ የመነሻ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡
- ስዕልን ከርዕሱ ጋር አዛምደው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሀሳቦች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- የትምህርቱን ይዘት ሲያቀርቡ የአካቶ ትምህርትን ይተግብሩ፡፡
- የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን ከ3-5 ደቂቃ ባሉ ጊዜያት ውስጥ ይተግብሯቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ተማሪዎች በሚገነዘቡበት ፍጥነት ልክ ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡
- በተማሪው መፅሐፍ የቀረቡ ስዕሎችን በማየት ተስማሚ ታሪኮችን በመፍጠር ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡

## አቶ ኑረዲንና ቤተሰባቸው

አቶ ኑረዲን የሐዋና የሙሐመድ አባት ናቸው፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን ልጃቸው ሙሐመድ ከትምህርት ቤት ጠፍቶ መጣ፡፡ አቶ ኑረዲንም በልጃቸው ሙሐመድ ድርጊት በጣም ተቆጡ፡፡

| |
|---|
| አቶ ኑረዲን ምን ሚያደርጉ ይመስላችኋል ? ገምቱ ? |

ከዚያም ሙሐመድን በቤተሰብ መካከል አስቀምጠው መከሩት፡፡ ሙሐመድም ከአሁን በኋላ እንዲህ አይነት ጥፋት ዳግም አልፈፅምም አለ፡፡ ትምህርት ቤት በአግባቡ እሄዳለሁ፡፡ እናንተንም ስላስከፋኋችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ አላቸው፡፡ ቤተሰቦቹም ይቅርታ አደረጉለት፡፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ታሪኩ እየተነበበ እያለ ለተጠየቁት ጥያቄ የመለሱት መልስ (ግምታቸው) ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፤ ያረጋግጡ፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

## ☞ተተኳሪ ፊደል

መምህር፡-

- አዳዲስ ሆሄያትን ያስተዋውቋቸው፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልና ዳራዊ እውቀታቸውን ታሳቢ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የፊደላቱን ቅርፅ ያንብቡላቸው፡፡
- የሆሄያትን ቅርፆች በፊደል ካርታ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው፡፡
- ድምፆችን በከንፈር እንቅስቃሴ እንዴት እንደሚያውቁ ያድርጓቸው፡፡
- ድምፅን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሳዩዋቸው፡፡
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን ያቅርቡላቸው፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው የሚሰሯቸው ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

## ⊶ቃላት

መምህር፡-

- ተዘውታሪ ቃላትን እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ስዕል በማየት የተዘውታሪ ቃላትን ስም እንዲጠሩ/ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ቃላትን ከስዕሎች ጋር እንዲያዛምዱ እድል ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው (በሚመልሱበት ወቅት ያድንቋቸው)
- አዳዲስ ሆሄያትን ያስተዋውቋቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ አዳዲስ ሆሄያትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡

- አዳዲስ ሆሄያትን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልና ዳራዊ እውቀት ታሳቢ ያድርጉ።
- የሆሄያቱን ቅርፅ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው።
- ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በካርቶን፣ በፊደል ካርድ፣.... ከቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው።
- አዳዲስ ሆሄያትን በጭብጨባ እንዲለዩ ያድርጓቸው።

ምሳሌ:-

- ፊደል ሲሆን አንድ ጊዜ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው።
- ቃል ሲሆን በውስጡ ባሉት ሆሄያት ልክ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው።

ሀ. “በ” የሚለው ሆሄ ስለሆነ አንድ ጊዜ ያጨበጭባሉ።

ለ. “በር” የሚለው ቃል ስለሆነ በውስጡ ባሉት ሆሄያት ልክ ሁለት ጊዜ ያጨበጭባሉ።

(በዚህ አይነት መልኩ ሌሎችንም ፊደላትና ሆሄያት እያስጠሩ በማጨብጨብ እንዲለዩ ያስደርጉ።)

- በቃላቱ ውስጥ ባሉት ፊደላት መጠን እንዲያጨበጭቡ እያስደረጉ ፊደላቱን እንዲለዩ ያድርጉ።
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን ያቅርቡላቸው።
- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ወይም የሚጀምሩ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን በመመስረት ለተማሪዎች ያሳዩዋቸው።

➢ የሚከተሉት ቃላት መነሻቸውን በተመሳሳይ ድምፅ “በ” የተመሰረቱ ናቸው።

1. በር
2. በሶ

(በዚህ አይነት መልኩ ተማሪዎች በሌሎች አዳዲስ ሆሄያት በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን እንዲናገሩ ወይም ቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው። ምላሽ ሲሰጡም በማበረታታት ያድንቋቸው።)

- በሚጠራው ባለሁለት ሆሄ ቃል መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ያለውን ድምፅ/ ሆሄ ለይተው እንዲጠሩ ያድርጉ

ምሳሌ:-

ቀባ (በሚለው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ “ቀ” ነው።)

ናቀ (በሚለው ባለሁለት ሆሄ ቃል የመድረሻ ድምፅ “ቀ” ነው።)

( በዚህ አይነት መልኩ ከጠ-ነ ባሉት ሆሄያት የተመሰረቱን ባለሁለት ሆሄ ቃል የመነሻና የመድረሻ ድምፅ እንዲለዩ ያርጓቸው።)

- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ያደረጉ የክፍልና የቤት ስራዎችን ያሰሯቸው
- የፊደላቱን ዘሮች የሚለዩባቸውን ሁኔታዎች እየፈጠሩ የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች እያዘጋጁ ይስጧቸው

- ሌሎች የማስተማር ዘዴዎችን በመተግበር ተተኳሪ ሆሄያቱን ለተማሪዎች ማድረስ ይችላሉ፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ወይም በቤታቸው ውስጥ የሚሰሯቸው ስራዎችን ያሰሯቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

✓ አዳዲስ ፊደላቱን ደጋግመው እንዲፅፉ ያርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ______________________________

በ ቀ

______________________________

(እንዲህ እያደረጉ ሌሎችንም ፊደላት በነጠብጣብና በመደበኛው አፃፃፍ እየፃፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡)

✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡- ______________________________

በር በሶ ቀዳ

______________________________

( በሌሎችም ሆሄያ የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግበሩ፡፡)

✓ አዳዲስ ፊደላትን በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲረስሱ ያድርጓቸው

✓ አዳዲስ ፊደላትን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣..... ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው

✓ ተተኳሪ ፊደላቱን በተለያዩ እርሳሶች ወይም ቀለማት እያከበቡ እንዲፅፉ ወይም ቀለም እንዲቀቡ ይዘዟቸው፡፡

✓ ድምፆችን በከንፈር እንቅስቃሴ እንዴት እንደሚያውቁ ያድርጓቸው፡፡

✓ ድምፅን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሳዩዋቸው፡፡

✓ በአየር ላይ፣ በወለል ላይ፣ በግድግዳ ላይ፣ ..... ፊደላቱን በመፃፍ ያለማምዷቸው፡፡

✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሁለት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው

✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም ቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይስጧቸው

✓ ባለሁለት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው

✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያረጉ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡

✓ ፊደላቱንና ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ

✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው

## ማዳመጥ

መምህር፡-

- የዕለቱን ትምህርት አላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ስዕሎቹን እንዲገምቱ የመነሻ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡
- ስዕልን ከርዕሱ ጋር አዛምደው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሀሳቦች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- የትምህርቱን ይዘት ሲያቀርቡ የአካቶ ትምህርትን ይተግብሩ፡፡
- የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን ከ3-5 ደቂቃ ባሉ ጊዜያት ውስጥ ይተግብሯቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ተማሪዎች በሚገነዘቡበት ፍጥነት ልክ ያንብቡላቸው፡፡
- በንበባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡
- በተማሪው መፅሐፍ የቀረቡ ስዕሎችን በማየት ተስማሚ ታሪኮችን በመፍጠር ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡

# ስለሺና ተሽከርካሪ ወንበሩ

ስለሺ የአካል ጉዳተኛ የሆነ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ እናትና አባቱ ትምህርቱን በሚገባ እንዲማር ያበረታቱታል፡፡ ለመንቀሳቀሻ የሚያስፈልገውንም ተሽከርካሪ ወንበር ያቀርቡለታል፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡)

## ማዳመጥ

# ኪሩቤልና ፍቅርተ

ኪሩቤልና ፍቅርተ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ናቸው፡፡ፍቅርተ አይነስውር ናት ፡፡ ቢሆንም ከወንድሟ ጋር አብረው ይጫወታሉ፡፡ አብረው ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ እህና ወንድም የመሆናቸውን ያህል በጣም ይዋደዳሉ፡፡ እናታቸውን በስራ ያግዛሉ፡፡ ሱቅ በመሄድም እናታቸው

የምትፈልገውን እቃ ገዝተው ይመጣሉ፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡)

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር እንዲያዛምዱና የራሳቸውን ሀሳብ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ ከምዕራፉ ዋነኛ ርዕስ ከሆነው "ቤተሰብ" ከሚለው ርዕስ ጋር የተገናኙ መጠሪያ ስሞችን እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ የፅህፈት ፅነሰ ሀሳብ የሆኑትን ቋሚ መስመር፣ አግድም መስመር፣ ስላች መስመር፣ ግራና ቀኝ ቅንፍ እና ቀለበት መስመርን በመለየት ደጋግመው ለመፃፍ ተሞክሯል፡፡ ከዚህም ሌላ ፊደላትን ባለአንድ እግር፣ ባለሁለት እግር፣ ባለሶስት እግር እና እግር አልባ ሆሄያትን ለመለየት ተሞክሯል፡፡

በተጨማሪም ተተኳሪ የሆኑ አዳዲስ ፊደላት ከ"በ-ቀ" ያሉትን ሆሄያት እስከነዘራቸው እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በነዚሁ ፊደላት ባለሁለት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡ እነዚህን ፊደላት በፊደል ካርድ፣ በካርቶን፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በቃላት ፋይል፣ .... እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ሁለት
# ቤት

የምዕራፉ ትምህርት አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ፡-

- ካዳመጡት ምንባብ መልዕክቱን ይረዳሉ፤
- በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶችን ቅርፃቸውን በማየት ስማቸውን ይጠራሉ
- የሆሄያትን መሠረታዊ ቅርፅ ይለያሉ፤
- አዳዲስ ሆሄያትን ወይም ድምፆችን ያነባሉ፤
- ባለሁለት ሆሄ ቃላትን ይፅፋሉ ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርት ድምፅ ግንዛቤ
- የተዘውታሪ ቃላት ጥናት
- ምንበብ
- በትክክል መፃፍ
- ድምፀት

## ማዳመጥ

መምህር፡-

- የዕለቱን ትምህርት አላማ ያስተዋውቁ፡፡
- ስዕሎቹን እንዲገምቱ የመነሻ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡
- ስዕልን ከርዕሱ ጋር አዛምደው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የሚገምቷቸውን አንዳንድ ሀሳቦች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- የትምህርቱን ይዘት ሲያቀርቡ የአካቶ ትምህርትን ይተግብሩ፡፡
- የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን ከ3-5 ደቂቃ ባሉ ጊዜያት ውስጥ ይተግብሯቸው፡፡
- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡን በተመጠነ ድምፅና ተማሪዎች በሚገነዘቡበት ፍጥነት ልክ ያንብቡላቸው፡፡
- በንባብ ጊዜ ላይ ያለውን ጥያቄ ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡
- በተማሪው መፅሐፍ የቀረቡ ስዕሎችን በማየት ተስማሚ ታሪኮችን በመፍጠር ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡

# እኔ ማን ነኝ?

ሰዎች ይኖሩብኛል፡፡ ከተለያዩ ቁሳቁሶች እሰራለሁ፡፡ ከሳር፣ ከቆርቆሮ፣ ከሸራ፣ ከሲሚንቶ ወይም ከብሎኬት፣ ከሳጠራ፣ወዘተ. እገነባለሁ፡፡ እንደምሰራበት ቀሳቁስም ስያሜዬን ይሰጡኛል፡፡ በርካታ ቁሳቁሶችንም በውስጤ ይዣለሁ፡፡ ሰዎችም በውስጤ ይኖራሉ፡፡ የሚኖሩብኘን ሰዎችንም ከፀሐይ፣ ከብርድ፣ ከዝናብ፣ ከአስፈሪ አውሬ፣ ከጠላት… እከላከላለሁ፡፡ የገነቡኝ ሰዎችም ውስጤን እንደምሰጣቸው አገልግሎቶች የመኝታ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ የመመገቢያ፣ የእቃ፣
የልጆች እና የአዋቂዎች መቀመጫ፣ የማጥኛ፣ የመፀዳጃ፣ ወዘተ እየተባልኩ በተለያዩ ክፍሎች እከፈላለሁ፡፡ ቀን ወጥተው ስራቸውን ጨርሰው ሲመለሱ ከቦታዬ ሳልንቀሳቀስ ያገኙኛል፡፡ ያለምንም ስጋት ያርፉብኛል፡፡ ከጎረቤቶቻቸው ጋር እየተጠራሩ ደስታቸውንም ሆነ ሀዘናቸውን ይካፈሉብኛል፡፡ የሚገለገሉባቸውን ቁሳቁሶች የሳሎን፣ የመኝታ፣ የወጥ ቤት እቃዎች እያሉ እየከፋፈሉ በውስጤ ያለምንም ስጋት ያኖሩብኛል፡፡ የመኝታ፣ የዕቃ፣ የመፀዳጃ፣ የመመገቢያ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ ወዘተ. እየተባልኩ በተለያዩ ክፍሎች እከፈላለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ?

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ተማሪዎች ያዳመጡትን ታሪክ መልዕክት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- በታሪኩ "እኔ ማን ነኝ?" በሚል የቀረበው ታሪክ የሚገልፀው ስለምን እንደሆነ ያዳመጡትን መነሻ በማድረግ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የሰጡትን ምላሽ መነሻ በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 🕮ንባብ

### መምህር፡-

- ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደላቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያርጓቸው፡፡
- የቃላት ፋይል በመጠቀም ወይም በአካባቢያቸው የተፃፉ ነገሮችን በማሳየት ተተኳሪ ፊደሎችን በቡድን ወይም በጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተተኳሪ ፊደላቱን በጣታቸው እየጠቆሙ ለጓደኞቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## ➢ ተተኳሪ ፊደል

መምህር፡-

- አዳዲስ ሆሄያትን ያስተዋውቋቸው፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልና ዳራዊ እውቀታቸውን ታሳቢ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የፊደላቱን ቅርፅ ያንብቡላቸው፡፡
- የሆሄያትን ቅርፃች በፊደል ካርታ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው፡፡
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን ያቅርቡላቸው፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው የሚሰሯቸው ስራዎችን ያሰሯቸው፡፡

## ቃላት

መምህር፡-

- ተዘውታሪ ቃላትን እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ያለውን ስዕል በማየት የተዘውታሪ ቃላትን ስም እንዲጠሩ/ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ቃላትን ከስዕሎች ጋር እንዲያዛምዱ እድል ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው (በሚመልሱበት ወቅት ያድንቋቸው)
- አዳዲስ ሆሄያትን ያስተዋውቋቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ አዳዲስ ሆሄያትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- አዳዲስ ሆሄያትን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልና ዳራዊ እውቀት ታሳቢ ያድርጉ፡፡
- የሆሄያቱን ቅርፅ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በካርቶን፣ በፊደል ካርድ፣.... ከቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው፡፡
- አዳዲስ ሆሄያትን በጭብጨባ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡-

- ፊደል ሲሆን አንድ ጊዜ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡
- ቃል ሲሆን በውስጡ ባሉት ሆሄያት ልክ እንዲያጨበጭቡ ያድርጓቸው፡፡

ሀ. “ጠ” የሚለው ሆሄ ስለሆነ አንድ ጊዜ ያጨበጭባሉ፡፡

ለ. “ጠጣ” የሚለው ቃል ስለሆነ በውስጡ ባሉት ሆሄያት ልክ ሁለት ጊዜ ያጨበጭባሉ፡፡

(በዚህ አይነት መልኩ ሌሎችንም ፊደላትና ሆሄያት እያስጠሩ በማጨብጨብ እንዲለዩ ያስደርጉ፡፡)

- በቃላቱ ውስጥ ባሉት ፊደላት መጠን እንዲያጨበጭቡ እያስደረጉ ፊደላቱን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን ያቅርቡላቸው፡፡
- በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ ወይም የሚጀምሩ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን በመመስረት ለተማሪዎች ያሳዩዋቸው፡፡

➢ የሚከተሉት ቃላት መነሻቸው በተመሳሳይ ድምፅ "ጠ" የተመሰረቱ ናቸው፡፡

1. ጠቡ
2. ጠባ
3. ጠብ

➢ የሚከተሉት ቃላት መድረሻቸው በተመሳሳይ ድምፅ "ረ" የተመሰረቱ ናቸው፡፡

1. ቀረ
2. ናረ
3. ማረ

- (በዚህ አይነት መልኩ ተማሪዎች በሌሎች አዳዲስ ሆሄያት በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን እንዲናገሩ ወይም ቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው፡፡ ምላሽ ሲሰጡም በማበረታታት ያድንቋቸው፡፡)
- በሚጠራው ባለሁለት ሆሄ ቃል መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ያለውን ድምፅ/ሆሄ ለይተው እንዲጠሩ ያድርጉ

ምሳሌ፡-

መቶ (በሚለው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ "መ" ነው፡፡)

ጣመ (በሚለው ባለሁለት ሆሄ ቃል የመድረሻ ድምፅ "መ" ነው፡፡)

( በዚህ አይነት መልኩ ከጠ-ነ ባሉት ሆሄያት የተመሰረቱንን ባለሁለት ሆሄ ቃል የመነሻና የመድረሻ ድምፅ እንዲለዩ ያርጓቸው፡፡)

- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ያደረጉ የክፍልና የቤት ስራዎችን ያሰሯቸው

- የፊደላቱን ዘሮች የሚለዩባቸውን ሁኔታዎች እየፈጠሩ የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች እያዘጋጁ ይስጧቸው

- ሌሎች የማስተማር ዘዴዎችን በመተግበር ተተኳሪ ሆሄያቱን

ለተማሪዎች ማድረስ ይችላሉ፡፡

- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ወይም በቤታቸው ውስጥ የሚሰሯቸው ስራዎችን ያሰሯቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ አዳዲስ ፊደላቱን በነጠብጣብና በመደበኛ መስመር ደግመው እንዲፅፉ ያርጓቸው፡፡

  ምሳሌ፡- ________________________________________________

  ጠ መ ረ ጠ መ ረ

  ________________________________________________

  (እንዲህ እያደረጉ ሌሎችንም ፊደላት በነጠብጣብና በመደበኛው አፃፃፍ እየፃፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡)
- ✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

  ምሳሌ፡- ________________________________________________

  ጠጣ መጣ ረዳ

  ________________________________________________

  ( በሌሎችም ሆሄያ የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግብሩ፡፡)

- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲረስሱ ያድርጓቸው
- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣

  ከመፅሐፋቸው፣..... ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው
- ✓ ተተኳሪ ፊደላቱን በተለያዩ እርሳሶች ወይም ቀለማት እያከበቡ እንዲፅፉ ወይም ቀለም

  እንዲቀቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በአየር ላይ፣ በወለል ላይ፣ በግድግዳ ላይ፣ ..... ፊደላቱን በመፃፍ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሁለት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም ቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች

  አዘጋጅተው ይስጧቸው
- ✓ ባለሁለት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያረገ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡
- ✓ ፊደላቱንና ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ
- ✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው

## 👂 ማዳመጥ

# አናጢው

ሳሙኤል በአናጢነት ሙያ ጎበዝ ነው፡፡ በስራው ብዙ ሰዎች ይደሰታሉ፡፡ የሚሰራቸው ቤቶች ጥራት አላቸው፡፡ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ቤቶችን ይሰራል፡፡ በሚሄድባቸው ቦታዎች የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች ይዞ ይገኛል፡፡ መዶሻ ፣ መጋዝ፣ ሜትር፣ ... ከሱ አይለዩም፡፡ አንድ ቀን ከስራ ቆይቶ ወደቤቱ ሲመለስ ጓደኛው ከቤቱ ጣሪያ ላይ ወጥቶ ያየዋል፡፡

ሳሙኤል ምን የሚያደርግ ይመስላችኂል?

ሳሙኤል ጓደኛውን ትቶት መሄድ አልፈለገም፡፡ በሙያው አገዘው፡፡ ጓደኛውም ስላደረገለት እገዛ በጣም አመሰገነው፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡በተጨማሪ ከአዳመጡት አንዳንድ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡)

## 👂 ማዳመጥ

# የእኛ ቤተሰብ

እኔና እህቴ ከወላጆቻችን ጋር በአንድ ቤት እንኖራልን፡፡ በቤታችን ውስጥ ጥሩ ፍቅር አለ፡፡ አባታችን ማታ ማታ ተረት ያወራልናል፡፡ እኛም የሚነግረንን ተረት በጥሞና እናዳምጣለን፡፡ እናታችንም ከእኛ ጋር አብራ ተቀምጣ ታዳምጣለች፡፡ ሁሌም መልካም ስነ ምግባርን የሚያስተምሩ ተረቶችን ይነግረናል፡ጉበዝ እንድንሆን ዘወትር ይመክረናል፡፡ እኔና እህቴ በእቅድ እናጠናለን፡፡ አባታችንም ቤተሰቡ መተሳሰብ እንዳለበት ይነግረናል፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡ በተጨማሪ ከምንባቡ ከአዳመጡት አንዳንድ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር እንዲያዛምዱና የራሳቸውን ሀሳበ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ ከምዕራፉ ዋነኛ ርዕስ ከሆነው “ቤት” ከሚለው ርዕስ ጋር የተገናኙ ቁሶችን መጠሪያ ስያሜ እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ተተኳሪ የሆኑ አዳዲስ ፊደላት ከ“ጠ-ነ” ያሉትን ሆሄያት እስከነዘራቸው እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በነዚሁ ፊደላት ባለሁለት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡ እነዚህን ፊደላት በፊደል ካርድ፣ በካርቶን፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በቃላት ፋይል፣ .... እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ሶስት
# ትምህርት ቤት

❖ የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-

- ስዕልን በማየት ታሪኩን ይገምታሉ፤
- የሚነበብ ታሪክን በማዳመጥ መልዕክቱን ይገልፃሉ፤
- ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ተዘውታሪ ቃላትን ይለያሉ፤
- አዳዲስ ሆሄያትን ያነባሉ፤
- ድምፅን ከሆሄያት ጋር ያዛምዳሉ፤
- ባለሶስት ሆሄ ቃላት ይመሰርታሉ፤

➢ የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መረዳት
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትምዕርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማንበብ
- ፅህፈት
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

*መምህር፦*

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ የዕለቱን ትምህርት ታሪክ ርዕስ ለተማሪዎች ይንገሯቸው፡፡
- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ❖ ከተማሪዎች መካከል ፍቃደኛ የሆነ/ የሆነች ተማሪ በማስነሳት ርዕሱን ያስነብቡ፤ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ስዕል ተመልክተው ከርዕሱ ጋር አዛምደው ግምታቸውን እንዲያጠናክሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸውና ታሪኩ ከመነበቡ በፊት የነበራቸው ግምት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡

# የትምህርት ቤታችን የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ

ያሬድ፣ ሰሚራ፣ ኮኬትና ሰሚር የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አራቱም የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ አባል ናቸው፡፡ ሰሚራ የክበቡ ተጠሪ ናት፡፡ ሁሉም በወጣላቸው ፕሮግራም መሰረት ጠዋትና ማታ አበቦችንና አትክልቶችን ዉሃ ያጠጣሉ፤ ይንከባከባሉ፡፡ በነዚህ ተማሪዎች አማካኝነት የትምህርት ቤቱ ግቢ ዉብና ማራኪ ሆነ፡፡ የክበቡ ሃላፊ መምህርና ርዕሰ መምህር የትምህርት ቤቱ ዉበት እንዲደምቅ አስተዋፅኦ ባደረገው ክበብ በተመለከተ ውይይት አካሄዱ፡፡ በክበቡ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎችን አመሰገኑ፡፡ ርዕሰ መምህሩም የአባላቱን ስም ዝርዝር ወሰዱ፡፡

***ርዕሰ መምህሩ የክበቡን አባላት ስም ዝርዝር የወሰዱት ለምን ይመስላችኋል?***

በጣም መልካምና ጥሩ ስራ ስለሰሩ የተለያዩ ሽልማቶችንና የምስክር ወረቀቶችን በሰንደቅ አላማ አከባበር ስነ ስርዓት ላይ ሰጧቸው፡፡ እነሱም በሰሩት ስራና በተደረገላቸው ሽልማት በጣም ተደሰቱ፡፡ ሌሎች ተማሪዎችም እነሱን በማየት በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ክበቦች ውስጥ በመሳተፍ የተሻለ ስራ ለመስራት ወሰኑ፡፡

## አዳምጦ መናገር

*መምህር፦*

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- (ሀሳባቸውን ይቀበሏቸው)

## ተዘውታሪ ቃላት

መምህር፡-

- ከትምህርት ቤት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተዘውታሪ ቃላትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ስሞችን (መምህር፣ ደብተር፣ መፅሐፍ፣ ዳስተር፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ ቾክ፣ ተማሪ፣ ወንበር፣....) ለይተው እንዲናገሩ ያበረታተቷቸው፡፡
- ስዕሎችን እያዩ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

## ንባብ

## መምህር፡-

- በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ተተኳሪ ቃላቱን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በማሳየት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደላቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያርጓቸው፡፡
- የቃላት ፋይል በመጠቀም ወይም በአካባቢያቸው የተፃፉ ነገሮችን በማሳየት ተተኳሪ ፊደሎችን በቡድን ወይም በጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተተኳሪ ፊደላቱን በጣቸው እየጠቆሙ ለጓደኞቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- መሠረታዊ ሆሄያቱን በጣታቸው እየጠቆሙ ከፍ ባለድምፅ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## ☞ ተተኳሪ ፊደል

መምህር፡-

- አዳዲስ ሆሄያትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያስተዋውቋቸው፡፡
- አዳዲስ ፊደላትን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን ዳራዊ አመጣጥ እና የትምህርት አቀባበል ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ፡፡
- በትምህርታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች ካሉ በመለየት የተለየ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የፊደላቱን ቅርፅ የሚለዩባቸውን ስልቶች ቀያይረው ያንብቡላቸው/ ያቅርቡላቸው፡፡
- የሆሄያትን ቅርፆች በፊደል ካርታ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ቀርፀው ያሳዩዋቸው፡፡
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያቅርቡላቸው፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው የሚለማመዱባቸውን ስራዎች ይስጧቸው፡፡

## ⊶ ቃላት

መምህር፡-

- ያለፈውን ትምህርት መከለስ

በምዕራፍ ሶስት የቀረቡትን ተተኳሪ ፊደላት ከማቅረብዎ በፊት በምዕራፍ ሁለት ባስተማሯቸው ፊደላት አራት ቃላትን ( በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ፣ በባለቀለም ወረቀት ላይ ፅፈው) ያቅርቡላቸው፡፡ የሚመሰረቱት ቃላት በመጀመሪያ ወይም በመጨረሻ ላይ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ይሁኑ (በምሳሌነት የቀረቡት ቃላት የተመሰረቱት በ"አ" መነሻ እና በ"ና" መድረሻ ሆሄ ነው)፡፡

| ምሳሌ፡- | | |
|---|---|---|
| | 1. አፍ | 1. ፋና |
| | 2. አሳ | 2. ቁና |
| | 3. አለ | 3. ናና |
| | 4. አባ | 4. ቀና |

( በዚህ አይነት መንገድ ሌሎችን ተተኳሪ ሆሄያት በመነሻ እና በመድረሻ ላይ እያስገቡ ባለሁለት ሆሄ ቃላትን እየመሰረቱ ያሳዩዋቸው፡፡ )

- በእያንዳንዱ ተተኳሪ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን ያስለዩ፡፡
- በተተኳሪ ድምፆች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመጥራት ድምፆችን ያስለዩ፡፡
  ምሳሌ፡- በ "ከ" የሚጀምሩ ባለሶስት ሆሄ ቃላት "ከበበ፣ ከበረ፣ ከደነ፣ .....
  በ "ካ" የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃል "ዋርካ፣ ሰበካ፣ በረካ፣ ....
  ( በዚህ መልኩ ሌሎችንም ሆሄያት በቃላት ውስጥ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በማስገባት ድምፆችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡)
- የተተኳሪ ፊደሎችን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው እየጠቀሙ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- በቃሉ ውስጥ ባሉት ሆሄያት ልክ ተማሪዎች በማጨብጨብ ሆሄያቱን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

  ምሳሌ፡- "ከበበ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደላት ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎችን በፊደላቱ ልክ ሶስት ጊዜ ያስጨብጭቡ፡፡

- መጨረሻቸው ተመሳሳይ የሆኑ ድምፅ ያላቸውን ቃላት በማስጠራት ሙዚቃ ወይም ምት እንዲፈጠር ደጋግመው በማስጠራት ሆሄያቱን እንዲለዩ ያስደርጉ፡፡
  ምሳሌ፡- ማራኪ፣ ሰባኪ፣ ተተኪ፣ .....
- ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡
- ቅርፃችን (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣.... ) በማሳየት ተማሪዎች ስያሜውንና ድምፁን እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ አዳዲስ ሆሄያትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ቅርፁን ከድምፁ ጋር በማዛመድ ያለማምዷቸው፡፡

# ማጣመርና መነጠል

| መነጠልና ማጣመር |
|---|
| ይህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ተማሪዎቹ (ልጆቹ) ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡ |
| ቃላትን ማጣመር፡- ሲባል ቃላቱ የተመሰረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሃዶች በአንድ ድምፅ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይጠሯቸዋል፡፡ |
| ቃላትን መነጠል፡- ሲባል ደግሞ ተጣምረው የተፃፉ ፊደላትን ወይም ሆሄዎችን ለየብቻ (ነጣጥለው) ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደ አነስተኛ አሃዶች ይነጣጥላሉ፤ ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሃዶች ለይተው ያነባሉ፡፡ |

- ከላይ የቀረበውን ፅንሰ ሃሳብ በቃል ካስረዷቸው በኋላ ምሳሌ ይስጧቸው
- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

ማጣመር

| መነጠል | | | ማጣመር |
|---|---|---|---|
| ገ | በ | ረ | ገበረ |
| ወ | ሰ | ደ | ወሰደ |
| ከ | በ | በ | ከበበ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደሎች በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፊደሎቹ “ ገ፣ በ እና ረ” ናቸው፡፡ ሲጣመሩ የሚመሰረተው ባለሶስት ሆሄ ቃል “ገበረ” ይሆናል፡፡

( ሌሎችንም እንደዚህ በተናጠል እየጠሩና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

መነጠል

| ማጣመር | መነጠል | | |
|---|---|---|---|
| ወፈረ | ወ | ፈ | ረ |
| ከበረ | ከ | በ | ረ |
| ገበሬ | ገ | በ | ሬ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በመነጠል ሆሄያቱን እንዲጠሩ፤ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቃሉ “ወፈረ” ነው፡፡ ፊደሎቹ ተነጣጥለው ሲነበቡ “ ወ፣ ፈ እና ረ” የሚሉት ሶስት ሆሄያት ናቸው፡፡

( ሌሎችንም እንደዚህ ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን እየጠሩ እንዲነጣጥሉ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

✓ አዳዲስ ፊደላቱን በነጠብጣበውና በመደበኛ መስመር ደግመው እንዲፅፉ ያርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ______________________________

ገ ወ ከ ገ ወ ከ

______________________________

(እንዲህ እያደረጉ ሌሎችንም ፊደላት በነጠብጣብና በመደበኛው አፃፃፍ እየፃፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡)

✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡- ______________________________

ወፈረ ገበረ ከበረ

______________________________

( በሌሎችም ሆሄያ የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግብሩ፡፡)

✓ አዳዲስ ፊደላትን በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲፅፉ ያድርጓቸው

✓ አዳዲስ ፊደላትን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣.....

ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው

✓ ተተኳሪ ፊደላቱን በተለያዩ እርሳሶች ወይም ቀለማት እያከበቡ እንዲፅፉ ወይም ቀለም እንዲቀቡ ይዘዟቸው፡፡

- ✓ በአየር ላይ፣ በወለል ላይ፣ በግድግዳ ላይ፣ ..... ፊደላቱን እንዲፅፉ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሶስት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም ቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይስጧቸው
- ✓ ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡
- ✓ መሠረታዊ ሆሄያትንና ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፤ ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የቃል ክፍሎች የሚባሉትን የክፍል ደረጃውን ታሳቢ ባደረጉ መልኩ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ከቃል ክፍሎችም ውስጥ ስሞችንና ግሶችን ይጠቀሙ፡፡
- ✓ በተተኳሪ ሆሄያቱ ስሞችንና ግሶችን በመመስረት ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡-

| ስሞች | ግሶች |
|---|---|
| 1. በቆሎ | 1. ሰበረ |
| 2. ዝሆን | 2. ከበበ |
| 3. ሜላት | 3. ዘመረ |

- ✓ ተማሪዎች በተማሯቸው ተተኳሪ ሆሄያት ባለሶስት ሆሄ የሆኑ ስሞችንና ግሶችን እንዲመሰርቱ እድል ይስጧቸው፡፡

## 👂 ማዳመጥ

# አርፋጁ ተማሪ

ሰላምና አቤል ጓደኛሞች ናቸው፡፡ የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው፡፡ ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት አብረው ይሄዳሉ፡፡ አቤል አንድ ቀን አረፈደ፡፡ ሰላምም ሲቆይባት የትምህርት ሰዓት እንዳያረፍድባት ጥላው ሄደች፡፡ አቤልም እየሮጠ ሲመጣ የትምህርት ቤቱ በር ተዘግቷል፡፡ የአንደኛው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው፡፡ መማሪያ ክፍል ውስጥ እንደገባ ቦርሳውን ሳያስቀምጥ ሰላምን ለምን ጥለሽኝ መጣሽ አላት ? የሁለቱ ጭቅጭቅ ቀጠለ፡፡ የመምህራቸውንም መግባት አላስተዋሉም ነበር፡፡

*** መምህራቸው ምን የሚሉ ይመስላችኋል?***

መምህራቸው ምን ያጨቃጭቃችኋል ብለው ጠየቋቸው? አንተስ ለምን አረፈድክ አሉት? አቤልም በፍጥነት የመማሪያ ቁሳቁሶቼን ሳላስተካከል በመተኛቴና እንቅልፍ ጥሎኝ ነው፡፡ መምህራቸውም ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት አለማድረግ እና በፕሮግራም አለመመራት ጥሩ አይደለም፡፡ ከዚህ በኋላ በእቅድ መመራት አለብህ፡፡ አሁን ሰላምን ይቅርታ ጠይቃት አሉት፡፡

# አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- (ሀሳባቸውን ይቀበሏቸው)

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡)

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ ማነገር ታሪኮች ቀርበዋል ፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ታሪክ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተተኳሪ ቃላት እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ተተኳሪ የሆኑ አዳዲስ ፊደላት ከ"ገ - የ - ዘ" ያሉትን ሆሄያት እስከነዘራቸው እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በነዚሁ ፊደላት ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡እነዚህን ፊደላትበፊደል ካርድ፣ በካርቶን፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በቃላት ፋይል፣ በጭብጨባ….. እንዲለ ዩተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ መሰረታዊ ሆሄያትን በደብተራቸው፣ በግድግዳ ፣ በወለል ወይም በእጃቸው በአየር ላይ መፃፍ ተለማምደዋል፡፡ እንዲሁም በተተኳሪ ሆሄያትን በመጠቀም ስምና ግስ የሆኑቃላትን መስርተዋል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18 ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ አራት
# ጓደኞሞች

❖ የምዕራፉ የትምህርት ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ፡-

- የሚያዳምጡትን ምንባብ መልዕክቱን ይገልፃሉ፤
- ስዕልን በማየት ታሪክን ይገምታሉ፤
- ተዘውታሪ ቃላትን ይለያሉ፤
- ለተለመዱ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፤
- አዳዲስ ሆሄያትን ወይም ድምፆችን ያነባሉ፤
- ድምፆችንና ሆሄያትን ያዛምዳሉ

የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡-

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ የዕለቱን ትምህርት ታሪክ ርዕስ ለተማሪዎች ይንገሯቸው፡፡
- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ❖ ከተማሪዎች መካከል ፍቃደኛ የሆነ/ የሆነች ተማሪ በማስነሳት ርዕሱን ያስነብቡ፤ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ስዕል ተመልክተው ከርዕሱ ጋር አዛምደው ግምታቸውን እንዲያጠናክሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸውና ታሪኩ ከመነበቡ በፊት የነበራቸው ግምት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

## ሁለቱ ጓደኞሞች

ነዒማና ካሌብ መጫወት ይወዳሉ፡፡ ትምህርት ቤት በእረፍት ሰዓታቸው ገመድ ዝላይ፣ ሴማክሴ፣ እግር ኳስ፣ አኩኩሉ፣ እና ሌሎች ጫዎታዎችን ይጫወታሉ፡፡ አንድ ቀን ነዒማ ካሌብን ‹‹ማን ብዙ መዝለል ይችላል?›› እንወዳደር አለችው፡፡ ካሌብም በሀሳቧ ተስማማ፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ ዘለሉ፡፡ ጨዋታው ቀጠለ፡፡ ካሌብ በፍጥነት ሲዘል ገመዱ ጠልፎት ወደቀ፡፡

*** ካሌብ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ***

ነዒማስ ምን የምታደርግ ይመስላችኋል?

ነዒማ ፈጥና በቅርብ ላሉት መምህሮቿ አሳወቀች፡፡ መምህሮቿም የትምህርት ቤቱን የጤና ክበብ ተጠሪ አስጠሩ፡፡ ለካሌብ የመጀመሪያ እርዳታ አደረጉለት፡፡ ጓደኞሞቹ ተያይዘው ወደ መማሪያ ክፍላቸው ሄዱ፡፡ የአማርኛ ትምህርት መምህራቸው እያስተማሩ ነበር፡፡ መምህራቸውም ምን እንደሆኑ ጠየቋቸው፡፡የተፈጠረውን ሁሉ ነገሯቸው፡፡ ጓደኞቻቸው አዘኑ፡፡መምህራቸው ለሁሉም ተማሪ ስትጫወቱ ራሳችሁን በማይጎዳ መልኩ መሆን እንዳለበት መከሯቸው፡፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- (ሀሳባቸውን ይቀበሏቸው)

## ተዘውታሪ ቃላት

መምህር፡-

- ከጓደኝነት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተዘውታሪ ቃላትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ በጓደኝነት ውስጥ የሚገኙ ጨዋታዎችንና ተግባሮችን (መሃረቤን ያያችሁ፣ ሴማክሴ፣ የገመድ ዝላይ፣ ጥምጥሞሽ(ቴዘር)፣ አብሮ መመገብ፣ ማጥናት፣ መወያየት፣ መሄድ፣ መማር፣....) ለይተው እንዲናገሩ ያበረታተቷቸው፡፡
- ስዕሎችን እያዩ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

## ንባብ

መምህር፡-

- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጨርሱ ቃላትን በዜማ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉትን ድምፆች በፍጥነት ያስነብቧቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ተተኳሪ ቃላቱን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በማሳየት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደላቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በቅልጥፍና እንዲያነቡ ያርድጓቸው፡፡
- የቃላት ፋይል በመጠቀም ወይም በአካባቢያቸው የተፃፉ ነገሮችን በማሳየት ተተኳሪ ፊደሎችን በቡድን ወይም በጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተተኳሪ ፊደላቱን በጣቸው እየጠቆሙ ለጓደኞቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- መሠረታዊ ሆሄያቱን በጣታቸው እየጠቆሙ ከፍ ባለድምፅ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍል ደረጃቸው ያለውን ትምህርታዊ ፅሑፍ በማሚቶ ንባብ፣ በህብረት ንባብ፣ በትብብር ንባብ፣ በጥንድ ንባብ፣ ከከሌላ ሰው ጋር ማንበብ እና በፀጥታ ንባብ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## ተተኳሪ ፊደላትን መከለስ

መምህር፡-

- ➢ በምዕራፍ አራት የሚቀርቡትን ተተኳሪ ፊደላት ከማቅረብዎ በፊት በምዕራፍ ሶስት ላይ በቀረቡት ተተኳሪ ፊደላት አስር ቃላትን በመመስረት/ በማቅረብ ትምህርቱን ያስታውሷቸው፡፡
- ➢ ከመሰረቷቸው ቃላት ውስጥ አምስቱ በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ይሁኑ፤ አምስቱ ደግሞ በተለያዩ ተተኳሪ ድምፆች የሚጨርሱ ይሁኑ፡፡

ምሳሌ፡-

| በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ቃላት | በተለያዩ ድምፅ የሚጨርሱ ቃላት |
|---|---|
| ከበበ | ሰበከ |
| ከበረ | ዘለለ |
| ከበደ | ዘገየ |
| ከሰረ | በቆሎ |
| ከደነ | ሰረዘ |

(በዚህ አይነት መንገድ ሌሎችን ተተኳሪ ሆሄያት በመነሻ እና በመድረሻ ላይ እያስገቡ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን እየመሰረቱ ያሳዩዋቸው፡፡)

- ➢ ተማሪዎች በተመሳሳይ/ በተለያዩ ድምፆች የሚጨርሱን ቃላት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ☞ ተተኳሪ ፊደል

መምህር፡-

- አዳዲስ ሆሄያትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያስተዋውቋቸው፡፡
- በትምህርታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች ካሉ በመለየት የተለየ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የፊደላቱን ቅርፅ የሚለዩባቸውን ስልቶች ቀያይረው ያንብቡላቸው/ ያቅርቡላቸው፡፡
- የሆሄያትን ቅርፆች በፊደል ካርታ፣ በባለቀለም ወረቀት፣በቅርፃ ቅርፅ፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ቀርፀው ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ተተኳሪ ድምፆች/ሆሄያት በጭብጨባ እየቆጠሩ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- አዳዲስ ሆሄያትን በባለሶስት ሆሄ ቃላት ውስጥ ለይተው እንዲያመለክቱ ያድርጓቸው፡፡
- ድምፅን ከሰውነት እንቅስቃሴ ጋር በማዋሃድ ያሳዩዋቸው፡፡
- በከንፈር እንቅስቃሴ ድምፆችን እንዲለዩ ያለማምዷቸው፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው የሚለማመዱባቸውን ስራዎች ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡-**

- በእያንዳንዱ ተተኳሪ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን ያስለዩ፡፡
- በተተኳሪ ድምፆች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመጥራት ድምፆችን ያስለዩ፡፡
  ምሳሌ፡- በ "ጭ" የሚጀምሩ ባለሶስት ሆሄ ቃላት "ጭፈራ፣ ጭልፋ፣ ጭጋግ፣ .....
  በ "ኝ" የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃል "አገኝ፣ ተመኝ፣ ተናኝ፣ ....
  (በዚህ መልኩ ሌሎችንም ሆሄያት በቃላት ውስጥ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በማስገባት ድምፆችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡)
- የተተኳሪ ፊደሎችን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያስመስርቱ፡፡

- በቃሉ ውስጥ ባሉት ሆሄያት ልክ ተማሪዎች በማጨብጨብ ሆሄያቱን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

  ምሳሌ፡- "ጫጩት" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደላት ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎችን በፊደላቱ ልክ ሶስት ጊዜ ያስጨብጭቡ፡፡

- መጨረሻቸው ተመሳሳይ የሆኑ ድምፅ ያላቸውን ቃላት በማስጠራት ሙዚቃ ወይም ምት እንዲፈጠር ደጋግመው በማስጠራት ሆሄያቱን እንዲለዩ ያስደርጉ፡፡
  ምሳሌ፡- መፍጫ፣ ዋንጫ፣ ቁንጫ፣ .....
- ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡
- ቅርፆችን (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣.... ) በማሳየት ተማሪዎች ስያሜውንና ድምፁን እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ አዳዲስ ሆሄያትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ቅርፁን ከድምፁ ጋር በማዛመድ ያለማምዷቸው፡፡
- በተተኳሪ ፊደላት ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

**መነጠልና ማጣመር**

ይህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ተማሪዎቹ (ልጆቹ) ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡

ቃላትን ማጣመር፡- ሲባል ቃላቱ የተመሰረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሃዶች በአንድ ድምፅ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይጠሯቸዋል፡፡

ቃላትን መነጠል፡- ሲባል ደግሞ ተጣምረው የተፃፉ ፊደላትን ወይም ሆሄዎችን ለየብቻ (ነጣጥለው) ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደ አነስተኛ አሃዶች ይነጣጥላሉ፤ ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሃዶች ለይተው ያነባሉ፡

- ከላይ የቀረበውን ፅንሰ ሃሳብ በቃል ካስረዷቸው በኋላ ምሳሌ ይስጧቸው
- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

# ማጣመር

| መነጠል | | | ማጣመር |
|---|---|---|---|
| ሃ | ም | ሳ | ሃምሳ |
| ዓ | ር | ማ | ዓርማ |
| ጃ | ኬ | ት | ጃኬት |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደሎች በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፊደሎቹ “ ሃ፣ ም እና ሳ” ናቸው፡፡ ሲጣመሩ የሚመሰረተው ባለሶስት ሆሄ ቃል “ሃምሳ” ይሆናል፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ በተናጠል እየጠሩና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

# መነጠል

| ማጣመር | መነጠል | | |
|---|---|---|---|
| ዘበኛ | ዘ | በ | ኛ |
| ኮርቻ | ኮ | ር | ቻ |
| ዋንጫ | ዋ | ን | ጫ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በመነጠል ሆሄያቱን እንዲጠሩ፤ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቃሉ “ዋንጫ” ነው፡፡ ፊደሎቹ ተነጣጥለው ሲነበቡ “ ዋ፣ ን እና ጫ” የሚሉት ሶስት ሆሄያት ናቸው፡፡

( ሌሎችንም እንደዚህ ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን እየጠሩ እንዲነጣጥሉ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡

ተ ገ ኘ = ተገኘ

ጨ መ ረ = ጨመረ

ሀ ብ ል = ሀብል

(በዚህ መልኩ ሌሎች ተተኳሪ ፊደሎችን ከፊደል ካርድ፣ ከቅርፃ ቅርፅ፣ ከካርቶን፣ … ላይ በመፈለግና በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ

## ✍ጽሕፈት

**መምህር፡-**

- ✓ አዳዲስ ፊደላቱን በነጠብጣብና በመደበኛ መስመር ደግመው እንዲፅፉ ያርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡-
___
ኘ ኚ ጨ ጮ ቸ ቼ ኘ ጨ ቸ
___

(እንዲህ እያደረጉ ሌሎችንም ፊደላት በነጠብጣብና በመደበኛው አፃፃፍ እየፃፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡)

- ✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡-
___
ጨርቅ ተመኘ ቸኮለ
___

( በሌሎችም ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግብሩ፡፡)

- ✓ ትክክለኛውን የፊደል አጣጣል በማሳየት ፊደላቱን እንዲቀርፁ ያድርጉ፡፡
- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲረስሱ ያድርጓቸው
- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣…..

ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው

- ✓ ተተኳሪ ፊደላቱን በተለያዩ እርሳሶች ወይም ቀለማት እያከበቡ እንዲፅፉ ወይም ቀለም እንዲቀቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በአየር ላይ፣ በወለል ላይ፣ በግድግዳ ላይ፣ ….. ፊደላቱን እንዲፅፉ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ የሆሄያቱ ድምፅ ሲጠራ ተማሪዎች ድምፁን የሰሙትን ሆሄ ጣታቸውን በመጠቀም በአየር ላይ ወይም በግድግዳ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሶስት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይስጧቸው
- ✓ ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡
- ✓ መሠረታዊ ሆሄያትንና ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፤ ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የክፍል ደረጃውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ማድረግ

ምሳሌ፡-

1. በረኛ
2. ተገኘ
3. ጫጩት
4. ሀብል
5. ሾርባ

- ✓ ተማሪዎች በተማሯቸው ተተኳሪ ሆሄያት ባለሶስት ሆሄ የሆኑ ስሞችንና ግሶችን እንዲመሰርቱ እድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የቤተሰብ ዛፍ በማሰራትና የቤተሰብ ስሞችን በማስፃፍ ስሞችን እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡






(ስዕሉን በደብተራቸው እንዲስሉ በማድረግ በሳጥኑ ውስጥ የቤተሰብ አባላት (እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣...) ስምን ተማሪዎች እንዲፅፉ ያድርጓቸው)

## ማዳመጥ

## እውነተኛ ጓደኛ

ከነቢኒያም ግቢ ብዙ ዛፎች አሉ፡፡ ቢኒያም ግን የአቮካዶውን ዛፍ በጣም ይወደዋል ፡፡ ከዛፉ ስር ሳር ስላለ ይተኛል፡፡ አንዳንድ ቀን ከዛፉ ቅርንጫፎች ላይ ወጥቶ ይጫወታል፤ ፍሬዎቹ ይረግፋሉ፡፡ ትንንሾቹ ቅርንጫፎች ይሰባበራሉ ፡፡ የቢኒያም አባት ሁልጊዜ ሲያዩት "አረ ተው ልጄ ጓደኛህን አታሰቃየው ይደርቃል እኮ!" ይሉታል ፡፡

*** ቢኒያም ምን የሚል ይመስላችኋል?***

ቢኒያም ግን አባዬ ዛፍ እኮ ነው ምንም አያወራም፤ አይናገርም፤ አይጫወትም ፤ እንዴት ጓደኛዬ ይሆናል? ይላል፡፡ ቢኒያም ዛፉ ላይ ያሉትን ፍሬዎች በሙሉ ማርገፉን ቀጠለ፡፡ ቀስ በቀስ ሳሮቹ ጠወለጉ፡፡ ዛፉ ደረቀ፡፡ አንድ ቀን ጧት ሲነሳ ዛፉ ወድቆ አገኘው፡፡ በጣም ደነገጠ፡፡ አባቱ የነገረውን አስታውሶ ተንበርክኮ ዛፉን አቅፎ አለቀሰ፡፡

(ምንጭ፡- ዳንኤል ወርቁ (2011) እውነተኛ ጓደኛ፡፡ ከሚለው የህፃናትን የንባብ ክህሎት ለማሳደግ ታስቦ ከተዘጋጀ መፅሐፍ ተሸሽሎ የተወሰደ)፡፡

## አዳምጦ መናገር

**መምህር፡-**

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡)

## የቃላት ፍቺ

**መምህር፡-**

- ተማሪዎች መፅሐፉ ላይ የቀረቡትን የተለመዱ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
  ምሳሌ፡-

  1. ቆየ = ዘገየ፣ አረፈደ
  2. ደመረ = ጨመረ፣ በአንድ ላይ አደረገ
  3. ማራኪ = ዉብ፣ ሳቢ፣ ቆንጆ
  4. ተማረ = አወቀ

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ታሪክ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተተኳሪ ቃላት እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ተተኳሪ የሆኑ አዳዲስ ፊደላት ከ"ኘ- ጀ" ያሉትን ሆሄያት እስከነዘራቸው እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በነዚሁ ፊደላት ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡ እነዚህን ፊደላት በፊደል ካርድ፣ በካርቶን፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በቃላት ፋይል፣ በጭብጨባ.... እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ መሰረታዊ ሆሄያትን በደብተራቸው፣ በግድግዳ ፣ በወለል ወይም በእጃቸው በአየር ላይ መፃፍ ተለማምደዋል፡፡ እንዲሁም ተተኳሪ ሆሄያትን በመጠቀም ቃላትን መስርተዋል፡፡ የተለመዱ ቃላትን ፍች መስጠት ችለዋል፡፡ ቃላትን በማጠመርና በመነጣጠል አሳይተዋል፡፡ የቤተሰብ ዛፍን በመስራት የቤተሰብ አባላትን መጥራት ችለዋል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ አምስት
# ተክሎች

የምዕራፉ ትምህርት አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ምንባቡን በማዳመጥ መልዕክቱን ይገልፃሉ፤
- ፊደላትን/ ድምፅን ይለያሉ፤
- ድምፅን ከሆሄ ጋር ያዛምዳሉ፤
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፤
- ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ይፅፋሉ፤
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤

የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡- የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ታሪክ ርዕስ ለተማሪዎች ይንገሯቸው፡፡
- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን፣ ስዕሉን እና ቁልፍ ቃላትን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸውና ታሪኩ ከመነበቡ በፊት የነበራቸው ግምት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

# የተክሎች ጥቅም

ተክሎች ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው፡፡ ከጠቀሜታቸው ውስጥ ለምግብነት፣ ለቁሳቁስ መስሪያነት፣ ለመጠለያ፣ ለልብስ፣ ለመዳህኒትና ለአካባቢ ውበት ለመስጠት ይጠቅማሉ፡፡ ለምግብነት የሚገለግሉ ተክሎች ሰላጣ፣ ጎመን፣ ማንጎ፣ ሙዝ፣ ሽንኩርት እና ሌሎችም አሉ ፡፡ለቁሳቁስ መስሪያነት የሚያገለግሉት ደግሞ ዕድ፣ ባህርዛፍ፣ ወይራ፣ ዋርካ፣ ወዘተ. ይገኛሉ፡፡ ጥጥ ደግሞ ለልብስ መስሪያነት ያገለግላል ፡፡

*** ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ ተክሎች ምን ምን ይመስሏችኋል?***

ጤናዳም፣ ነጭ ሽንኩርት ፣ ጥቁር አዝሙድ ፣ ዝንጅብል፣ ዳማከሴ እና ሌሎችም አሉ፡፡ እንደ አደይአበባና ፅጌረዳ አበባ ደግሞ አካባቢን ውበት ለመስጠት ያገለግላሉ፡፡ ስለዚህ ተክሎች ከሌሉ የሰው ልጆች ሁሉ በህይወት ለመኖር ይቸገራሉ፡፡ እነዚህን ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች መትከልና በአግባቡ መንከባከብ አለብን፡፡

# አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ በቃል የሚመልሱት ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
  1. ለምግብነት የሚያገለግሉት የተክል አይነቶች የትኞቹ ናቸው?
  2. ለመድኃኒትነት የምንጠቀምባቸው ተክሎች እነማን ናቸው?
- (ተማሪዎች ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡)

## ተዘውታሪ ቃላት

*መምህር፡-*

- ከተክሎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተዘውታሪ ቃላትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ በተክሎች ውስጥ የሚገኙ ስሞችን (ቆስጣ፣ ጎመን፣ አበባ፣….) ለይተው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስዕሎችን እያዩ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

## ንባብ

*መምህር፡-*

- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጨርሱ ቃላትን በዜማ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉትን ድምፆች በፍጥነት ያስነብቧቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ተተኳሪ ቃላቱን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በማሳየት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ተተኳሪ ፊደላቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በቅልጥፍና እንዲያነቡ ያርጓቸው፡፡
- የቃላት ፋይል በመጠቀም ወይም በአካባቢያቸው የተፃፉ ነገሮችን በማሳየት ተተኳሪ ፊደሎችን በቡድን ወይም በጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተተኳሪ ፊደላቱን በጣቸው እየጠቆሙ ለጓደኞቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- መሠረታዊ ሆሄያቱን በጣታቸው እየጠቆሙ ከፍ ባለድምፅ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍል ደረጃቸው ያለውን ትምህርታዊ ፅሑፍ በማሚቶ ንባብ፣ በህብረት ንባብ፣ በትብብር ንባብ፣ በጥንድ ንባብ፣ ከከሌላ ሰው ጋር ማንበብ እና በፀጥታ ንባብ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## ተተኳሪ ፊደላትን መከለስ

*መምህር፡-*

- ➢ በምዕራፍ አምስት የሚቀርቡትን ተተኳሪ ፊደላት ከማቅረብዎ በፊት በምዕራፍ አራት ላይ በቀረቡት ተተኳሪ ፊደላት አስር ቃላትን በመመስረት/ በማቅረብ ትምህርቱን ያስታውሷቸው፡፡
- ➢ ከመሰረቷቸው ቃላት ውስጥ አምስቱ በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ይሁኑ፤ አምስቱ ደግሞ በተለያዩ ተተኳሪ ድምፆች የሚጨርሱ ይሁኑ፡፡

ምሳሌ፡-

| በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ቃላት | በተለያዩ ድምፅ የሚጨርሱ ቃላት |
|---|---|
| ጭማቂ | መዋጮ |
| ጭረት | ወዳጅ |
| ጭጋግ | ቆንጆ |
| ጭልፋ | ጉባዔ |
| ጭፈራ | ድንች |

(በዚህ አይነት መንገድ ሌሎችን ተተኳሪ ሆሄያት በመነሻ እና በመድረሻ ላይ እያስገቡ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን እየመሰረቱ ያሳዩዋቸው፡፡)

➢ ተማሪዎች በተመሳሳይ/ በተለያዩ ድምፆች የሚጨርሱን ቃላት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ☞ ተተኳሪ ፊደል

*መምህር፡-*

- አዳዲስ ሆሄያትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያስተዋውቋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ የፊደላቱን ቅርፅ የሚለዩባቸውን ስልቶች ቀያይረው ያንብቡላቸው/ ያቅርቡላቸው፡፡
- የሆሄያትን ቅርፆች በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣በቅርፃ ቅርፅ፣ በካርቶን፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ቀርፀው ያሳዩዋቸው፡፡
- የተተኳሪ ፊደሉን ቅርፅ በማሳየት ፊደሉን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ተተኳሪ ድምፆች/ሆሄያት በጭብጨባ እየቆጠሩ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- አዳዲስ ሆሄያትን በባለሶስት ሆሄ ቃላት ውስጥ ለይተው እንዲያመለክቱ ያድርጓቸው፡፡
- በከንፈር እንቅስቃሴ ድምፆችን እንዲለዩ ያለማምዷቸው፡፡
- የተተኳሪ ፊደሎችን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣ …. እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ቅርፃችን (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣…. ) በማሳየት ተማሪዎች ስያሜውንና ድምፁን እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡
- ቅርፁን ከድምፁ ጋር በማዛመድ ያለማምዷቸው፡፡
- በመፅሐፉ የቀረቡትን ፊደላት መነሻ በማድረግ በክፍል ውስጥ ወይም በቤታቸው የሚለማመዱባቸውን ስራዎች ይስጧቸው፡፡
- በትምህርታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች ካሉ በመለየት የተለየ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

*መርጃ መሳሪያዎች፡-*

- የፊደል ገበታ
- ስዕሎች
- የፊደል ካርድ
- የቃላት ፋይል
- ቅርፃ ቅርፅ
- ካርቶን
- ባለቀለም ወረቀት
- ፊደላትንና ቃላትን በግድግዳ ላይ መለጠፍ
- የቃላት ጨዋታ

## ቃላት

*መምህር፡-*

- በእያንዳንዱ ተተኳሪ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን ያስለዩ፡፡
- በተተኳሪ ድምፆች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመጥራት ድምፆችን ያስለዩ፡፡

  ምሳሌ፡- በ "ሸ" የሚጀምሩ ባለሶስት ሆሄ ቃላት "ሸለመ፣ ሸቀለ፣ ሸማኔ፣ .....

  በ "ሸ" የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃል "አቡሸ፣ አብሸ፣ ፈሳሸ፣ ....

  (በዚህ መልኩ ሌሎችንም ሆሄያት በቃላት ውስጥ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በማስገባት ድምፆችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡)
- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያስመስርቱ፡፡
- በቃሉ ውስጥ ባሉት ሆሄያት ልክ ተማሪዎች በማጨብጨብ ሆሄያቱን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

  ምሳሌ፡- "ሹራብ" በሚለው ቃል ውስጥ ሶስት ፊደላት ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎችን በፊደላቱ ልክ ሶስት ጊዜ ያስጨብጭቡ፡፡
- መጨረሻቸው ተመሳሳይ የሆኑ ድምፅ ያላቸውን ቃላት በማስጠራት ሙዚቃ ወይም ምት እንዲፈጠር ደጋግመው በማስጠራት ሆሄያቱን እንዲለዩ ያስደርጉ፡፡

  ምሳሌ፡- ፈራሸ፣ ፍራሸ፣ ለባሸ፣ .....
- ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- በተተኳሪ ፊደላት ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## መነጠልና ማጣመር

ይህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ተማሪዎቹ (ልጆቹ) ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡

- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## ማጣመር

| መነጠል | | | ማጣመር |
|---|---|---|---|
| ሹ | ራ | ብ | ሹራብ |
| ን | ፁ | ህ | ንፁህ |
| ሻ | ን | ጣ | ሻንጣ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደሎች በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፊደሎቹ " ሹ፣ ራ እና ብ" ናቸው፡፡ ሲጣመሩ የሚመሰረተው ባለሶስት ሆሄ ቃል "ሹራብ" ይሆናል፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ በተናጠል እየጠሩና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## መነጠል

| ማጣመር | መነጠል | | |
|---|---|---|---|
| መያዣ | መ | ያ | ዣ |
| ሾርባ | ሾ | ር | ባ |
| ፅዮን | ፅ | ዮ | ን |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በመነጠል ሆሄያቱን እንዲጠሩ፤ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቃሉ "ሾርባ" ነው፡፡ ፊደሎቹ ተነጣጥለው ሲነበቡ " ሾ፣ ር እና ባ" የሚሉት ሶስት ሆሄያት ናቸው፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን እየጠሩ እንዲነጣጥሉ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡

ሾ ር ባ = ሾርባ

ቀ ረ ፀ = ቀረፀ

ሻ ወ ር = ሻወር

(በዚህ መልኩ ሌሎች ተተኳሪ ፊደሎችን ከፊደል ካርድ፣ ከቅርፃ ቅርፅ፣ ከካርቶን፣ ... ላይ በመፈለግና በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ አዳዲስ ፊደላቱን በነጠብጣብና በመደበኛ መስመር ደግመው እንዲፅፉ ያርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡-

ሸ ሼ ፀ ጼ ዠ ዤ ሸ ፀ ዠ

(እንዲህ እያደረጉ ሌሎችንም ፊደላት በነጠብጣብና በመደበኛው አፃፃፍ እየፃፉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡)

- ✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡-

ሹራብ ቀረፃ ፅዳት

(በሌሎችም ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሁለት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግብሩ፡፡)

- ✓ ትክክለኛውን የፊደል አጣጣል በማሳየት ፊደላቱን እንዲቀርፁ ያድርጉ፡፡
- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲረስሱ ያድርጓቸው
- ✓ አዳዲስ ፊደላትን በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣….. ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው
- ✓ ተተኳሪ ፊደላቱን በተለያዩ እርሳሶች ወይም ቀለማት እያከበቡ እንዲፅፉ ወይም ቀለም እንዲቀቡ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በአየር ላይ፣ በወለል ላይ፣ በግድግዳ ላይ፣ ….. ፊደላቱን እንዲፅፉ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ ሆሄው/ ድምፁ ሲጠራ ተማሪዎች የሰሙትን ድምፅ/ ሆሄ ጣታቸውን በመጠቀም በአየር ላይ፣ በግድግዳ ወይም በጠረጴዛ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ ድምፅን ከሆሄ ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሶስት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም ቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይስጧቸው
- ✓ ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡
- ✓ መሠረታዊ ሆሄያትንና ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፤ ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የክፍል ደረጃውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው ባለሶስት ሆሄ ቃል

እንዲመሰርቱ ማድረግ

ምሳሌ፡-

4. ህንፃ　　　　4. ቀረፀ

5. ሻወር　　　　5. ሾርባ

6. ድምፅ

- ✓ ተተኳሪ ፊደላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተ ነገሮችን እንዲፅፉ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ ስለዓረፍተ ነገር ምንነት ለክፍል ደረጃው ባማከለ መልኩ በአጭሩ ይግለጹላቸው

ምሳሌ፡-

1. አቡሽ ሾርባ ጠጣ፡፡
2. ፂዮን እርሳስ ቀረፀች፡፡
3. ተማሪዎች ችግኝ ተከሉ፡፡

(በተማሪው መፅሐፍ ባለው ትዕዛዝ መሠረት ሌሎች ነጠላ አረፍተነገሮችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

- ✓ የተለመዱ ፊደላትን በማገጣጠም ቃላትን ያስመስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| | እ | |
| በ | ራ | ድ |
| ሬ | ት | |

ምሳሌ፡- 1. በራድ

2. በሬ

3. እራት

4. ሬት

(በዚህ አይነት መንገድ በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትንና ሌሎች የቃላት ጨዋታ ጥያቄዎችን በመስጠት ቃላትን እያጣመሩ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡)

👂 **ማዳመጥ**

# ችግኝ መትከል

አንድ ቀን ሰአዳ ሁሉም ሰው አረንጓዴ አሻራውን ማሳረፍ አለበት ሲባል ሰማች፡፡ ሰአዳም አሻራዋን ለማሳረፍ ተነሳሳች፡፡ ከአባቷ ጋር ሄደች፡፡ አባቷን አንድ ችግኝ እንዲገዙላት ጠየቀቻቸው፡፡ አባቷም ገዙላት፡፡ ችግኟ እንዳይወድቅባት አጥብቃ ያዘችው፡፡ ከቦታው ደረሱ፡፡ ብዙ ሰዎች ለመትከል ደፋ ቀና ሲሉ ይታያሉ፡፡ ግማሾቹ ጉድጓድ ይቆፍራሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ችግኞቹን ጉድጓዱ ውስጥ እያስገቡ ይተክላሉ፡፡ ሰአዳም አባቷ በቆፈሩት ጉድጓድ ችግኟን ተከለች፡፡ አባቷ የማሸጊያውን ፌስታል ሳታላቅቅ ችግኙን ስትተክል አዩት፡፡

*** አባቷ ሰአዳን ምን የሚሏት ይመስሏችኋል?***

አባቷም ችግኝ ሲተከል በመጀመሪያ የማሸጊያው ፌስታል መላቀቅ አለበት፡፡ ከለበለዚያ የችግኙ ስሮች ወደ ሚፈልጉት ቦታ በመንቀሳቀስ ውሃና ምግብ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ውሃና ምግብ ካላገኙ ደግሞ ይደርቃሉ፡፡ ስለዚህ ችግኙ አያድግም ብለው መከሯት፡፡ የአባቷን ምክር ተቀለች፡፡ ከዚያም የተከለችውን ነቅላ እንደገና ማሸጊያውን አላቃ ተከለች፡፡ በየአመቱ ብዙ ችግኝ ለመትከል ወሰነች፡፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡

(ሌሎችን ተግባራት፤ንባብ፣ ተተኳሪ ፊደል፣ መፃፍ የሚሉትን ተግባራት ከዚህ በፊት በቀረበው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ በማድረግ ትምህርቱን ለተማሪዎች ያቅርቡላቸው፡፡)

## የቃላት ፍቺ

- በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የማዛመድ ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ የተለመዱ ቃላትን በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ታሪክ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተተኳሪ ቃላት እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ተተኳሪ የሆኑ አዳዲስ ፊደላት ከ"ሸ፣ ፀ፣ ዡ፣ ጸ፣ ፐ እና ቨ" የሚሉትን ሆሄያት እስከነዘራቸው እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በነዚሁ ፊደላት ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡ እነዚህን ፊደላት በፊደል ካርድ፣ በካርቶን፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በቃላት ፋይል፣ በጭብጨባ.... እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ መሰረታዊ ሆሄያትን በደብተራቸው፣ በግድግዳ፣ በወለል፣ ጠረጴዛ ወይም ጣታቸውን በመጠቀም በአየር ላይ መፃፍ ተለማምደዋል፡፡ እንዲሁም ተተኳሪ ሆሄያትን በመጠቀም ቃላትን መስርተዋል፡፡ የተለመዱ ቃላትን ፍች የሰጡ ሲሆን ቃላትን በማጠመርና በመነጣጠል አሳይተዋል፡፡ እንዲሁም በመነጣጠልና በማጣመር የለዩዋቸውን ቃላት በማንበብ እና በመፃፍ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ ተለማምደዋል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18

ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ስድስት
# የመንገድ ደህንነት

የምዕራፉ ትምህርት አላማዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአዳመጡትን ምንባብ መልዕክት ይገልፃሉ፤
- ቃላት ይመሰርታሉ፤
- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፤
- ከቃላት ላይ ቅጥያዎችን ይነጥላሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡- የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡

- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱንና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸው፡፡ ምንባቡን በመሀል ቆም ያድርጉና ቀጣዩ ሀሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡ ታሪኩ ከመነበቡ በፊት የነበራቸው ግምት ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ ከመንገድ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች በዜማ ያቅርቡላቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ታሪኮችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

# የትራፊክ ፖሊሷ ምክር

ሳምሶን በረከት እባላለሁ፡፡ ጓደኛዬ ደግሞ መሃመድ ሰኢድ ይባላል፡፡ ጓደኛሞች ስለሆንን ዘወትር ወደ ትምህርት ቤት አብረን እንሄዳለን፡፡ አንድ ቀን መንገዱ በመኪና ተጨናንቆ ደረስን፡፡ጓደኛዬን "እንዴት እናቋርጥ?" ጠየኩት፡፡ ጓደኛዬም "ችግር የለውም በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ እናቋርጣለን" አለኝ፡፡ በእግረኛ መንገድ እንዳናቋርጥ ተሽከርካሪዎች መጓዛቸውን አላቋረጡም፡፡ "የትራፊክ ፖሊሷን እንጠይቃት" አልኩት፡፡ ጓደኛዬም በሀሳቤ ተስማማ፡፡

*** የትራፊክ ፖሊሷን ምን ብለው የሚጠይቋት ይመስላችኋል? ***

"መንገድ ላይ ተሽከርካሪዎች በሚበዙበት ወቅት እግረኞች እንዴት ማቋረጥ አለባቸው?" ብለን ጠየቅናት፡፡ ትራፊኳም "የእግረኛ ማቋረጫን ከማቋረጣችሁ በፊት የትራፊክ መብራቱን ማየት አለባችሁ፡፡ አረንጓዴ ሲበራ ተሽከርካሪዎች ይጓዛሉ፤ ቢጫ ሲበራ በመስመር ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች ያልፋሉ፤ ቀይ ሲበራ ወይም የሰው ምስል ሲያሳይ ደግሞ እግረኞች ያቋርጣሉ" በማለት ነገረቻቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለታችንም የትራፊክ መብራትን በመጠቀም ሳንቸገር መንገዳችንን እንሻገራለን፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ በቃል የሚመልሱት ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
    1. እግረኞች መንገድ ከማቋረጣቸው በፊት የትራፊክ መብራት ማየት ያለባቸው ለምንድን ነው?
    2. የአረንጓዴ መብራት ምንን ይጠቁማል?
- (ተማሪዎች ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡)
- ከተማሪው መፅሐፍ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ከመንገድ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች በዜማ ያቅርቡላቸው፡፡

## 🔒 ተዘውታሪ ቃላት

መምህር፡-

- ከመንገድ ደህንነት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተዘውታሪ ቃላትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ በ መንገድ ደህንነት ጋር የተያያዙ ነገሮችን (መንገድ፣ የትራፊክ ፖሊስ፣ የእግረኛ ማቋረጫ(ዜብራ)፣ መኪና የትራፊክ መብራት፣....) ለይተው እንዲናገሩ ያበረታተቷቸው፡፡
- ስዕሎችን እያዩ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ከመንገድ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች በዜማ ያቅርቡላቸው፡፡

## 🗝 የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡
- በተተኳሪ ፊደላት ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ይህ ክፍል ተማሪዎች ቃላትን ለማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ተማሪዎቹ (ልጆቹ) ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡

▪ የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## ማጣመር

| መነጠል | | | ማጣመር |
|---|---|---|---|
| ወ | ተ | ት | ወተት |
| ው | ዳ | ሴ | ውዳሴ |
| ቤ | ት | ዎ | ቤትዎ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደሎች በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፊደሎቹ “ ወ፣ ተ እና ት” ናቸው፡፡ ሲጣመሩ የሚመሰረተው ባለሶስት ሆሄ ቃል “ወተት” ይሆናል፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ በተናጠል እየጠሩና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

▪ የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## መነጠል

| ማጣመር | መነጠል | | |
|---|---|---|---|
| አዛኘ | አ | ዛ | ኘ |
| ውርስ | ው | ር | ስ |
| ጫማዎ | ጫ | ማ | ዎ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በመነጠል ሆሄያቱን እንዲጠሩ፤ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቃሉ "አዛኘ" ነው፡፡ ፊደሎቹ ተነጣጥለው ሲነበቡ " አ፣ ዛ እና ኘ" የሚሉት ሶስት ሆሄያት ናቸው፡፡

( ሌሎችንም እንደዚህ ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን እየጠሩ እንዲነጣጥሉ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- በእያንዳንዱ ተመሳሳይ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመመስረት ያሳዩዋቸው፡፡
- በተተኳሪ ድምፆች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመጥራት ድምፆችን ያስለዩ፡፡

  ምሳሌ፡- በ "ወ" የሚጀምሩ ባለሶስት ሆሄ ቃላት "ወተት፣ ወገን፣ ወርቅ፣ .....

  (በዚህ መልኩ ሌሎችንም ሆሄያት በቃላት ውስጥ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በማስገባት ድምፆችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡)
- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያስመስርቱ፡፡
- ተማሪዎች የመጨረሻ ድምፃቸው ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፤ የመሰረቱትንም ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡

## ንባብ

## መምህር

- እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን አረፍተ ነገር ጥንድ ጥንድ እያደረጉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፤፤
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ፊደላት በደብተራቸው ላይ ደግመው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ፊደላት በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው፣..... ላይ በመፃፍ ቅርፃቸውን እንዲለዩ ያድርጓቸው
- ✓ በተተኳሪ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃል እየፃፉ ያሳዩዋቸው፡፡

  ምሳሌ፡-    ወርቅ    ዉበት    ጎንዎ

  (በሌሎችም ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃል በዚሁ መንገድ እያሳዩዋቸው ይተግብሩ፡፡)

- ✓ በመፅሐፉ ላይ የቀረቡትን ባለሶስት ሆሄ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- ✓ ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ወይም እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሠረት ባደረገ መልኩ ፊደላቱን መድረሻ በማድረግ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ወይም ቤታቸው ወስደው የሚለማመዱባቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይስጧቸው
- ✓ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡
- ✓ ቃላቱን በትክክል መፃፋቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፤ ያረጋግጡ፡፡
- ✓ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ የማበረታቻ ቃል ይስጧቸው፡፡
- ✓ የክፍል ደረጃውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የቃል ክፍሎችን ተጠቅመው ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ✓ የተጓደሉ ሆሄያትን በማሟላት ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የተለመዱ ፊደላትን በማገጣጠም ቃላትን ያስመስርቱ፡፡

(በዚህ አይነት መንገድ በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትንና ሌሎች የቃላት ጨዋታ ጥያቄዎችን በመስጠት ቃላትን እያጣመሩ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡)

## 👂 ማዳመጥ

# ከቤና ጓደኞቹ

ከቤ፣ ተሰማና ሲፈን የሚኖሩት አንድ ሰፈር ነው ። ወደ ትምህርት ለመሄድ ሁልጊዜ ይጠራራሉ። ተሰማ በጠዋት አይነሳም። እነሲፈን እሱን በመጠበቅ ሁልጊዜ ትምህርት ቤት አርፍደው ይደርሳሉ። በዚህ ምክንያት መምህራቸው በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ይሰጧቸው ነበር። አንድ ቀን ማስጠንቀቂያ በተሰጣቸው ማግስት በማርፈዳቸው በችኮላ መሮጥ ጀመሩ። ከትምህርት ቤቱ አጠገብ የመኪና መንገድ አለ። ከቤ ወላጆቹ በነገሩት መሰረት የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ካላገኘ ዝም ብሎ አያቋርጥም። ተሰማና ሲፈን በማርፈዳቸው ተደናገጡ። በዚህም የተነሳ የእግረኛ ማቋረጫ በሌለበት አቋረጡ። ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ይተላለፍ የነበረ ብስክሌት ሲፈንን ገጨውና ወደቀ ።

*** ሲፈን ምን ጉዳት የሚደርስበት ይመስላችኋል?***

ጉልበቶቹ ተላላጡ፤ ተሰማም እሸሻለሁ ሲል የመንገዱ ጠርዝ አደናቅፎት ወደቀ። እጆቹን ድንጋይ መታው። እግሮቹም ቆሰሉ። ከቤ የእግረኛ ማቋረጫ መንገዱን አቋረጦ ትምህርት ቤት ደረሰ። ክፍል ውስጥ ጓደኞቹን በማጣቱ ምን ሆነው ይሆን ብሎ ደነገጠ። ጓደኞቹ እያነከሱ መጡ። ከዚያም ከዛሬ ጀምሮ በእግረኛ ማቋረጫ ካልሆነ በቀር እንደማይሻገሩ ለራሳቸው ቃል ገቡ።

(መነሻ ሀሳብ፡-የብሔራዊ መንገድ ደህንነት አስተባባሪ ፅ/ቤት፣ 1996፣ 53)

## አዳምጦ መናገር

*መምህር፡-*

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው።
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው።
- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎችን ያሰሯቸው
- (ተማሪዎች ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው።)

## 🗝 ቃላት

መምህር፡-

- ቃላትን በማጣመርና በመነጠል ያሳዩዋቸው፤ ተማሪዎች ቃላትን በማጣመርና በመነጠል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያስመስርቱ፡፡
- ተማሪዎች የመጨረሻ ድምፃቸው ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፤ የመሰረቱትንም ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይስፃፉላቸው፡፡
- ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በፊደል ካርድ ላይ በተናጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትንና ቅጥያዎችን እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- ስለቅጥያ በአጭሩ ገለጻ ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- ቅጥያዎችን የያዘ ቅርፃ ቅርፅ ይጠቀሙ
- የፊደል ካርድ

## 🕮ንባብ

## መምህር

- እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን አረፍተ ነገር በቡድን እያደራጁ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍል ደረጃው ያለውን ትምህርታዊ ፅሑፍ በማሚቶ ንባብ፣ በህብረት ንባብ፣ በትብብር ንባብ፣ በጥንድ ንባብ፣ ከሌላ ሰው ጋር ንባብ እና በፅጥታ ንባብ እንደየሁኔታው እየቀያየሩ ያስነብቧቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## የቃላት ፍቺ

- ➢ በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ከትርጉማቸው ጋር በባለቀለም ወረቀት ላይ በመፃፍ ያቅርቡላቸው።
- ➢ የግድግዳ ላይ ቃላትን ከነፍቻቸው ያዘጋጁ፤ ተማሪዎች ቃላትን ከነፍቻቸው እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው።
- ➢ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ የተለመዱ ቃላትን በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ።
- ➢ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው።

| | | |
|---|---|---|
| መርጃ መሳሪያዎች፡- | - የቃላት ፋይል | - የግድግዳ ላይ ቃላት |
| | - ቻርት | - ቅርፃ ቅርፅ |

## ✍ ጽሕፈት

**መምህር፡-**

- ✓ በተማሪ መፃፍ ላይ የቀረቡትን ሆሄያት በማጣመር ባለ ሶስትና ባለሁለት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።
- ✓ ቃላትን በማጣመር ነጠላ አረፍተ ነገሮችን እንዲፅፉ ያለማምዷቸው።
- ✓ በተማሪው መፅሐፍ ባለው ትዕዛዝ መሠረት ሌሎች ነጠላ አረፍተነገሮችን እንዲሰሩ ያድርጉ።

## 🕮ንባብ

## መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ታሪክ እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ።
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው።
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው።
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ።

የማስተማሪያ ስልት፡- ዘዴዎችን እንደሁኔታው እየቀያየሩ ይተግብሩ።

| | |
|---|---|
| - ማሚቶ ንባብ | - ጥንድ ንባብ |
| - ህብረት ንባብ | - ፀጥታ ንባብ |
| - ትብብር ንባብ | |

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ታሪክ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተተኳሪ ቃላት እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

ተተኳሪ ሆሄያትን በመጠቀም ቃላትን መስርተዋል፡፡ የተለመዱ ቃላትን ፍች የሰጡ ሲሆን ቃላትን በማጣመርና በመነጣጠል አሳይተዋል፡፡ እንዲሁም በመነጣጠልና በማጣመር የለዩዋቸውን ቃላት በማንበብ እና በመፃፍ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ ተለማምደዋል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ሰባት
# ተረት

የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የአዳመጡትን ምንባብ ይተርካሉ፤
- በፅሑፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ፤
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፤
- አጫጭር አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፤
- ከቃላት ላይ ቅጥያዎችን ይነጥላሉ፤

የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

*መምህር፡- የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡*

- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ታኮችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

## ዶሮና ጭልፊት

በድሮ ጊዜ ጭልፊትና ዶሮ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ በጣም ከመቀራረባቸው የተነሳ ምግባቸውን በጋራ ይመገቡ ነበር፡፡ ዶሮ ግን ሁልጊዜ እንደ ጭልፊት መብረር ትመኝ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዶሮ ጭልፊትን ምነው እንዳንች በሰማይ ላይ በበረርኩ አለቻት፡፡ ጭልፊትም "ለምን አትሞክሪም እንደኔ ክንፍ አለሽ" አለቻት፡፡ ዶሮ ለመብረር ብትሞክርም አልሆነላትም፡፡ ጭልፊትም "አንዳንዴ ክንፎቼ ሲደክሙብኝ እሰፋቸዋለሁ፤ አንችም ክንፎችሽን ሰፍተሽ ለምን አትሞክሪም" አለቻት፡፡ ዶሮ ደስ አላት፡፡ቸኩላ "እባክሽ መርፌውን አውሽኝ መብረር እንድችል" አለቻት፡፡"እኔ ልሰጥሽ እችላለሁ፤ግን ከጣልሽብኝ መጣላታችን ነው" አለቻት፡፡ ዶሮ ቸኩላ "ግድ የለሽም ሰፍቼ ቶሎ እመልሳለሁ" አለች፡፡ ከችኮላዋ የተነሳ ስትደናበር ከጭልፊት የተዋሰችው መርፌ  ጠፋባት፡፡

**በሁለቱ መካከል ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?**

**ጭልፊት ዶሮን ምን የምትላት ይመስላችኋል?**

ጭልፌት መርፌዬን መልሽልኝ ብላ ስትመጣ ዶሮ ሮጣ ተደበቀች፡፡ ጭልፌት ስትሄድላት  የጠፋውን መርፌ ፍለጋ መሬቱን መጫር ጀመረች፡፡ እስካሁን ድረስ መርፌውን አላገኘችውም፡፡በዚህ ምክንያት በድንገት ጭልፊት ከመጣችባት ከነጫጩቶቿ ትደበቃለች፡፡ ጭልፊትም ዶሮን ካየች ዝም ብላ አታልፍም፡፡ በጠፋው መርፌ የተነሳ  ጭልፊትና ዶሮ እስከ ዛሬ ድረስ በጠብ ይኖራሉ  ይባላል፡፡

(ምንጭ፡- ዳንኤል ወርቁ፣ 2011፣ ዶሮና ጭልፊት ከሚለው መፅሐፍ ተቀንጭቦ የተወሰደ፡፡)

## አዳምጦ መናገር

*መምህር፡-*

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ከተማሪ መፅሐፍ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምፀጧቸውና የሚያውቁትን ታሪክ እርስ በርሳቸው እንዲነጋገሩ ያድርጉ፤ የተሻለውን ታሪክ ይምረጡ፡፡
- ከተመረጠው ታሪክ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡

## 🗝 የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-በቃላት ውስጥ ያሉ ድምፆችን በመነጠልና በማጣመር ያሳዩዋቸው፡፡ ያንብቡላቸው

- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- በተተኳሪ ፊደላት ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን በመነጠል ወይም በማጣመር እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

▪ የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## ማጣመር

| መነጠል | | | ማጣመር |
|---|---|---|---|
| ጨ | ረ | ታ | ጨረታ |
| ጨ | በ | ጣ | ጨበጣ |
| መ | ጥ | ጩ | መጥጩ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደሎች በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ፊደሎቹ “ጨ፣ ረ እና ታ” ናቸው፡፡ ሲጣመሩ የሚመሰረተው ባለሶስት ሆሄ ቃል “ጨረታ” ይሆናል፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ በተናጠል እየጠሩና እያጣመሩ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

▪ የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡

## መነጠል

| ማጣመር | መነጠል | | |
|---|---|---|---|
| ጪሰኛ | ጪ | ሰ | ኛ |
| ጭላዳ | ጭ | ላ | ዳ |
| ለዋጪ | ለ | ዋ | ጪ |

ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ ምሳሌ በማድረግ ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት በመነጠል ሆሄያቱን እንዲጠሩ፤ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቃሉ “ጭላዳ” ነው፡፡ ፊደሎቹ ተነጣጥለው ሲነበቡ “ ጭ፣ ላ እና ዳ” የሚሉት ሶስት ሆሄያት ናቸው፡፡

(ሌሎችንም እንደዚህ ተጣምረው የቀረቡ ቃላትን እየጠሩ እንዲነጣጥሉ ያለማምዷቸው፤ እነሱም እንዲሰሩ ያርጓቸው፡፡)

- በእያንዳንዱ ተመሳሳይ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመመስረት ያሳዩዋቸው፡፡

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን የመነጠልና የማጣመር ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ካሉ ድጋፍ ይስጧቸው፡፡

| መርጃ መሳሪያዎች፡- | የማስተማሪያ ስልቶች፡- |
|---|---|
| - የቃላት ፋይል | - የግል ስራ |
| - ቅርፃ ቅርፅ | - በቡድን ማደራጀት |
| - የፊደል ካርድ | - በጥንድ ማሰራት |

# የቃላት ፍቺ

## መምህር፡-

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ከትርጉማቸው ጋር በባለቀለም ወረቀት ላይ በመፃፍ ያቅርቡላቸው፡፡
- የግድግዳ ላይ ቃላትን ከነፍቻቸው ያዘጋጁ፤ ተማሪዎች ቃላትን ከፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ የተለመዱ ቃላትን በመስጠት ፍቻቸውን እንዲፈልጉ ያድርጉ፡፡
- በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

| መርጃ መሳሪያዎች፡- | | |
|---|---|---|
| | - የቃላት ፋይል | - የግድግዳ ላይ ቃላት |
| | - ቻርት | - ቅርፃ ቅርፅ |

## 🕮ንባብ

**መምህር፡-**እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን አረፍተ ነገር ጥንድ ጥንድ እያደረጉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

# ቅጥያዎችን መለየት

መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በፊደል ካርድ ላይ በተናጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- ቅጥያዎችን በመነጠልና በማጣመር እየሰሩ ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በመነጠል እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- በቃላት ላይ ቅጥያዎችን እየጨመሩ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ቃላትንና ቅጥያዎችን እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- - ቅጥያዎችን የያዘ ቅርፃ ቅርፅ ይጠቀሙ - ቻርት
- የፊደል ካርድ

## 🕮ንባብ

**መምህር፡-**

- እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን አረፍተ ነገር ጥንድ ጥንድ እያደረጉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ በእያንዳንዱ ተመሳሳይ ፊደሎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመመስረት ያሳዩዋቸው፡፡
- ✓ በተተኳሪ ድምፆች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ቃላትን በመጥራት ድምፆችን ያስለዩ፡፡

  ምሳሌ፡- በ "ጨ" የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላት "ተፈጨ፣ ተጋጨ፣ ፊልጬ፣ .....

  (በዚህ መልኩ ሌሎችንም ሆሄያት በቃላት ውስጥ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በማስገባት ድምፆችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡)

- ✓ በተመሳሳይ ድምፅ የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን ያስመስርቱ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የመጨረሻ ድምፃቸው ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፤ የመሰረቱትንም ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላትና ድምፆች እንዲጠሩ ያስደርጓቸው፡፡

## 👂 ማዳመጥ

# አንበሳና አይጥ

በድሮ ጊዜ አንድ አንበሳ በጫካው ውስጥ ምሳውን በልቶ ተኝቷል፡፡ አንድ ትንሽ አይጥ ስትጫወት ሳታስበው በአንበሳው ላይ በመጫወት ላይ እያለች፤ አንበሳው ድንገት ከእንቅልፉ ነቃና አፈፍ አድርጎ አንገራገረመባት፡፡

አንበሳው አይጧን ምን የሚያደርጋት ይመስላችኋል?

አይጧም በጣም ደንግጣ አትብላኝ፤ ‹‹እኔን በልተህ ምንም አልጠቅምህም፤ አንድ ቀን ውለታ እውልልሀለሁ›› ብላ ተማፀነችው፡፡ሀሀሀ… ውለታ ብሎ አንቺ አይጥ ጠግቤ ስላገኘሁሽ እድለኛ ነሽ ብሎ ለቀቃት፡፡ እሷም በደስታ ወደጨዋታዋ ተመለሰች፡፡ አንድ ቀን አንበሳው ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ሲያጓራ ሰማችው፡፡ አንባሰው ችግር ደርሶበታል መርዳት አለብኝ በማለት እየሮጠች ሄደች፡፡ እንደደረሰችም ወጥመዱን በስለታም ጥርሷ በጣጥሳ ከወጥመዱ እንዲወጣ አገዘችው፡፡ አንበሳውም በጣም ተደስቶ አይጥ ሆይ አመስግንሻለሁ፡፡ በጫካዬ ውስጥ እንደልብሽ መጫወት ትችያለሽ አላት፡፡

# አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎችን ያሰሯቸው
- (ተማሪዎች ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡)

## 🗝 የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን በመነጠል ወይም በማጣመር እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረቱ ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን የመነጠልና የማጣመር ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ካሉ ድጋፍ ይስጧቸው፡፡

## ✍ጽሕፈት

### መምህር፡-

- ✓ ተነጣጥለው የቀረቡ ቃላትን በማጣመር እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## የቃላት ፍቺ

### መምህር፡-

- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ከትርጉማቸው ጋር በባለቀለም ወረቀት ላይ በመፃፍ ያቅርቡላቸው፡፡
- የግድግዳ ላይ ቃላትን ከነፍቻቸው ያዘጋጁ፤ ተማሪዎች ቃላትን ከፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡
- የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ የተለመዱ ቃላትን በመስጠት ተቃራኒ ፍቻቸውን እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መርጃ መሳሪያዎች፡- | - የቃላት ፋይል | - የግድግዳ ላይ ቃላት |
| | - ቻርት | - ቅርፃ ቅርፅ |

## 📖ንባብ

### መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ታሪክ እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

የማስተማሪያ ስልት፡- ዘዴዎችን እንደሁኔታው እየቀያየሩ ይተግብሩ፡፡

- ማሚቶ ንባብ
- ህብረት ንባብ
- ትብብር ንባብ
- ጥንድ ንባብ
- ፀጥታ ንባብ

## ✍ ጽሕፈት

መምህር፡-

- ✓ ቃላትን መነሻ በማድረግ አረፍተ ነገር እንዲፅፉ ያለማምዷቸው፡፡
- ✓ ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር በማዛመድ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በሳጥን ውስጥ ያሉትን ቃላት በማጣመር አረፍተ ነገር እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

## 🕮ንባብ

## መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ዓ.ነገር እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የታሪክ ርዕሶችንም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ታሪክ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ታሪኮችን እንዲነጋገሩ ተደርጓል፡፡ የተሻለውን በመምረጥ የቃል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡

የተለመዱ ቃላትን ፍች የሰጡ ሲሆን ቃላትን በማጣመርና በመነጣጠል አሳይተዋል፡፡ እንዲሁም በመነጣጠልና በማጣመር የለዩዋቸውን ቃላት በማንበብ እና በመፃፍ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ የተለመዱ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ ተለማምደዋል፡፡ በተጨማሪም በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቅጥያዎችን በመነጠል ለማሳት ሞክረዋል፡፡

ከላይ በቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸው እንዲዳብር ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመዘን በተማሪው መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ተተኳሪ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግና የራስዎን መመዘኛ መንገድ እንዲሁም የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18

ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ስምንት
# ምግብ

የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ምንባቡን በማዳመጥ ዋናውን ሀሳብ ይናገራሉ፤
- የምግብ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፤
- ቃላትን በመነጠልና በማጣመር ያነባሉ፤
- የተለመዱ ቃላትን ያነባሉ፤

የምዕራፉ ይዘቶች

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡-

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ በቤታቸው የሚገኙ ምግቦችን እንዲናገሩ በቃል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ታሪኮችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

## የተመጣጠነ ምግብ

ሁለት ነፍሰ ጡ ር ሴቶች በአንድ የጤና ተቋም ውስጥ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ አንደኛዋ ብልህና የተማረች ስለሆነች የተመጣጠነ ምግብ ትመገባለች፡፡ ፅንሱም ሆነ እሷ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለፅንሱ እድገት የሚያስፈልገውን የምግብ አይነት በአግባቡ ትወስዳለች፡፡ በዚህም ምክንያት የምግብ ፍላጎቷ ጨምሯል፡፡ የፅንሱ እድገት በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ሌላኛዋ ግን በትምህርቷ ያልገፉችና በእለት ገቢዋ ዝቅተኛ ስለሆነች በሰዓቱ የተመጣጠነ ምግብ አትመገብም፡፡ ለፅንሱ የሚያስፈልገውን ምግብ በአግባቡ ስለማትወስድ የፅንሱ እንቅስቃሴና እድገትም ዝቅተኛ ሆነ፡፡ ሁለቱም የመውለጃ ጊዚያቸው ደረሰ፡፡ ለመውለድ ወደ ጤና ተቋም ሄዱ፡፡ የተመጣጠነ ምግብ የተመገበችዋ ሴት ጤናማ ስለነበረች በሰላም ተገላገለች፡፡

*** የተመጣጠነ ምግብ ያልተመገበችው ሴት ምን የምትሆን ይመስላችኋል? ***

የተመጣጠነ ምግብ ባለመመገቡዋ የደም ማነስ አጋጠማት፡፡ ህመሟ በረታባት፡፡ የደም ዓይነቷ ቶሎ አልተገኘም፡፡ ምጧ ጠነከረባት፡፡ በሐኪሞች ርብርብ ተገላገለች፡፡ ልጇም ኪሎዋ አነስተኛ ስለሆነች ማሞቂያ ክፍል አስገቡዋት፡፡ ባጠቃላይ ለአዋቂም ሆነ ለህፃናት የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ወሳኝ ነው፡፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ከተማሪ መፅሐፍ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

## የተለመዱ ቃላት

መምህር፡-

- የምግብ አይነቶችን የያዘ የሃሳብ ካርታ (ቻርት፣...) ይስሩ፡፡
  ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ ወይም ሁኔታ ላይ
  ተማሪዎች የሃሳብ ካርታውን ተመልክተው የምግብ አይነቶችን እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

## ትዕዛዝ፡- በምሳሌው መሠረት የምግብ አይነቶችን ያስሯቸው፡፡

ባህላዊ

- እንጀራ
- ቆጮ
- ክትፎ
- ገንፎ
- ሽሮ
- ዶሮ ወጥ

**የምግብ አይነቶች**

ዘመናዊ

- ፒዛ
- በርገር
- ፓስታ
- ማካሮኒ
- ሳንዱዊች
- ኬክ

## ቃላት

መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ ያሉ በመጀመሪያ እና በመጨረሻ ላይ የሚመጡ ድምፆችን በመለየት ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በምሳሌው መሠረት ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በመጀመሪያና በመጨረሻ ላይ የሚገኙ ድምፆች ተለይተው የተቀመጡባቸውን ቃላትና ሆሄያት በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ካሉ ድጋፍ ይስጧቸው፡፡

መርጃ መሳሪያዎች፡-

- የቃላት ፋይል
- ቅርፃ ቅርፅ
- የፊደል ካርድ

የማስተማሪያ ስልቶች፡-

- የግል ስራ
- በቡድን ማደራጀት
- በጥንድ ማሰራት

## የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን በመነጠል ወይም በማጣመር እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በመነጠልና በማጣመር ከለዩ በኂላ ድምፆቹ በደንብ እንዲሰሙ አድርገው እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- የተመረጡ ድምፆችን እየጠሩ እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በማጣመርና በመነጠል ሆሄያቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን የመነጠልና የማጣመር ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ታሳቢ ባደረገ መልኩ ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

| መርጃ መሳሪያዎች፡- | የማስተማሪያ ስልቶች፡- |
|---|---|
| - የቃላት ፋይል<br>- ቅርፃ ቅርፅ<br>- የፊደል ካርድ | - የግል ስራ<br>- በቡድን ማደራጀት<br>- በጥንድ ማሰራት |

## ቅጥያዎችን መለየት

መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎችና ቃላትን በፊደል ካርድ ላይ በተናጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- ቅጥያዎችን በመነጠልና በማጣመር እየሰሩ ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በመነጠል እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- - ቅጥያዎችን የያዘ ቅርፃ ቅርፅ ይጠቀሙ - ቻርት

- የፊደል ካርድ

## ✍ጽሕፈት

### መምህር፡-

- ✓ በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱ የቤተሰብ አባላት መጠሪያ ስሞችን (ለምሳሌ፡- እናት፣ አባት፣ እህት፣ አጎት፣ አያት፣ አክስት፣ወዘተ.) እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡-

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ታሪኩ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ታሪኩን ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ የታሪኩን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ታሪኮችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

## የዋሁ ቡጡ

ቡጡ ብዙ ጊዜ ሲርበው ያገኘውን ምግብ ይመገባል፡፡ አንድ ቀን እናቱ ገዝተው ያስቀመጡትን ቲማቲም ማዕድ ቤት አየ፡፡ቲማቲሙን አንስቶ እናቱ ሳያዩት ሳያጥብ በጥሬው በላው፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሆዱን ቆረጠው፡፡ ወዲያውኑ እንዳመመው ለአባቱ ተናገረ፡፡ አባቱም ወደ ጤና ተቋም ወሰዱት፡፡ የጤና ባለሙያውም ቡጡን በማረጋጋት ምን እንደሚሰማው ጠየቁት ፡፡ ቡጡም ሁሉንም ተናገረ፡፡ የሰገራ ምርመራ ተደረገለት፡፡

*** የሰገራ ምርመራው ውጤት ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ***

ሐኪሙ ቡጡንና አባቱን ጠርተው ውጤቱ የምግብ መበከል መሆኑን ነገሩዋቸው፡፡ ‹‹ንፅህናው የተጓደለ ምግብ ተመግቦ ሊሆን ይችላል አሉዋቸው፡፡ በጥሬያቸው የሚበሉ ምግቦችን በሚገባ ታጥበው መመገብ እንዳለባቸው፤የበሰሉ ምግቦችም ቢሆኑ በትኩስነታቸው መመገብ እንደሚገባቸው›› መከሩዋቸው፡፡ ለጊዜው ህመሙን የሚያስታግስለት መድሃኒት ሰጡት፡፡ በአግባቡ እንዲጠቀም ነገሩት፡፡ ቡጡና አባቱ የሐኪሙን ምክር ተቀብለው ተግባራዊ አደረጉ፡፡ ቡጡም ጤናው ተመለሰለት፡፡ ቡጡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ንፅህናው ያልተጠበቀ ምግብ አይመገብም፡፡

# አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ታሪኩ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ከተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

# 🕮ንባብ

# መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ በመጀመሪያ እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያድርጉ፤ ሚናቸውን እየተቀያየሩ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በጣት እየጠቆሙ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቀረበው የሀሳብ ካርታ ስር ለያይተው እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡

> የማስተማሪያ ስልት፡- ዘዴዎችን እንደሁኔታው እየቀያየሩ ይተግብሩ፡፡
>
> - ማሚቶ ንባብ
> - ህብረት ንባብ
> - ትብብር ንባብ
> - ጥንድ ንባብ
> - ፀጥታ ንባብ

## ✍ጽሕፈት

### መምህር፡-

- ✓ በሠንጠረዥ ውስጥ ተነጣጥለው የቀረቡ ሆሄያትን በማጣመር ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- ✓ በቃል ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን ቦታ በመለዋወጥ እና ፊደላትን በመቀነስ አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ ያስደርጉ፡፡

ምሳሌ፡- ቀመረ= ቀረ፣ መረቀ

ከመረ= መከረ፣ከረመ፣....

- ✓ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተመሳሳይ ስራዎችን እንዲሰሩ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ተከታታይ የሆነ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

## 🕮ንባብ

### መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን የምግብ ስሞች በመጀመሪያ እርስዎ አርዓያ በመሆን ድምፅዎን ቅላፄ በመለዋወጥ በማንበብ ያሳዩዋቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ እድል ይስጧቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## ✍ጽሕፈት

### መምህር፡-

- ✓ በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረበውን ምንባብ በማንበብ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን አውጥተው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡
- ✓ በምሳሌው መሠረት አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ፅፈው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በትክክል መስራት አለመስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- ✓ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የሰሩትን አረፍተ ነገሮች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፅፈው በትክክል መስራታቸውንና ስህተት ካለበት እርማት በመስጠት እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የምንባቡን ርዕሶችም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲናገሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ምንባብ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡

የተለመዱ ቃላትን በሃሳብ ካርታ ላይ በማስፈር የቃላት እውቀታቸውን አዳብረዋል፡፡በቃላት ውስጥ የመጀመሪያና የመጨረሻ ድምፆችን ለይተው ማሳየት ችለዋል፡፡ እንዲሁም በመነጣጠልና በማጣመር የለዩዋቸውን ቃላት በማንበብ እና በመፃፍ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ በጽሑፍ ውስጥ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መመስረት ተለማምደዋል፡፡ በተጨማሪም በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቅጥያዎችን በመነጠል ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ከዚህም ባሻገር በቃላት ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን ቦታ በመቀያየር አዳዲስ ቃላትን መስርተዋል፡፡

በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ይዘቶች ተግባራዊ በማድረግ የራስዎን መመዘኛ መንገድ እና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የግል ንፅህና አጠባበቅ

**የምዕራፉ አላማዎች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች:-

- ✓ ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክት በቃላቸው ያብራራሉ፤
- ✓ አዳዲስ ሆሄያትን በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን ይመሰርታሉ፤
- ✓ ድምፆችን በማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፤
- ✓ ከግል ንፅህና ጋር የተያያዙ አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ፤
- ✓ ባለሁለት ፊደል ቃላትን ይነጥላሉ፤ያጣምራሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## ማዳመጥ

መምህር፡-

- የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ከርዕሱ ተነስተው ምንባቡ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ትኩረታቸው ከርስዎ ጋር መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምንባቡን በመሃል ቆም በማድረግ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
- ምላሻቸውን እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ምንባቦችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

# በግል ንፅህና መጓደል የሚመጡ በሽታዎች

በንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች በርካታ ናቸው፡፡ የኮሮና ቫይረስ፣ ታይፎይድ፤ ኮሌራ፣ ታይፈስ፣ የአንጀት ተስቦ፣ ወ.ዘ.ተ. ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኮሮና ቫይረስ በዋናነት የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ ቫይረሱ ከሚተላለፍባቸው ዋነኛ መንገዶች ውስጥ ባልታጠበ እጅ አፍን ፣ አፍንጫን ና አይንን በመንካት ነው፡፡ ይህ ቫይረስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን ሁሉ የሚያጠቃ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በዕድሜያቸው የገፉ ሰዎችን በይበልጥ ያጠቃል፡፡

*** በሽታውን የምንከላከልባቸው መንገዶች ምን ምን ይመስሏችኋል? ***

ከመከላከያ መንገዶቹ ውስጥ አንዱና ዋነኛው የግል ንፅህናን መጠበቅ ነው፡፡ ይህ ሲባል እጃችንን በውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ፣ በጥሬያቸው የሚበሉ ምግቦችን በሚገባ አጥቦ መመገብ ፣ ቫይረሱ ከያዛቸው ሰዎች ጋር አካላዊ ንክኪ አለማድረግ፣ አካላዊ ርቀታችን መጠበቅ፣ የአፍና የአፍንጫ ጭንብል መጠቀም፣ የእጅ ማፅጃ አልኮል መጠቀም ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ምንባቡ እየተነበበ እያለ ለተጠየቁት ጥያቄ የመለሱት መልስ (ግምታቸው) ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፤ ያረጋግጡ፡፡
- ከተማሪ መፅሐፍ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

## ትዕዛዝ፡- ባዳመጣችሁት ምንባብና በምሳሌው መሠረት የሚከተለውን ሠንጠረዥ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

### በግል ንፅህና መጓደል የሚመጡ በሽታዎች

**የኮሮና በሽታ**

የሚተላለፍባቸው መንገዶች

- በትንፋሽ
- በመጨባበጥ
- ርቀትን ባለመጠበቅ
- ጭምብል አለመጠቀም

መከላከያ መንገዶች

- እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ
- አካላዊ ርቀትን መጠበቅ
- ጭምብል መጠቀም
- በጥሬያቸው የሚበሉ ምግቦችን አብስሎ መብላት

**የኮሌራ በሽታ**

የሚተላለፍባቸው መንገዶች

- ንፅህና አለመጠበቅ
- በተበከለ ምግብ
- በተበከለ ዉሃ
- በንክኪ

መከላከያ መንገዶች

- እጅን በአግባቡ በዉሃና በሳሙና መታጠብ
- ምግብን አብስሎ መጠቀም
- ውሃን አፍልቶ/ አክሞ መጠቀም

## ቃላት

መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ ያሉ በመጀመሪያ እና በመጨረሻ ላይ የሚመጡ ድምፆችን በመለየት ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በምሳሌው መሠረት ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በመጀመሪያና በመጨረሻ ላይ የሚገኙ ድምፆች ተለይተው የተቀመጡባቸውን ቃላትና ሆሄያት በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተዘውታሪ ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰረት ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- እገዛ የሚያስፈልጋቸው ካሉ ድጋፍ ይስጧቸው፡፡

| መርጃ መሳሪያዎች፡- | የማስተማሪያ ስልቶች፡- |
|---|---|
| - የቃላት ፋይል | - የግል ስራ |
| - ቅርፃ ቅርፅ | - በቡድን ማደራጀት |
| - የፊደል ካርድ | - በጥንድ ማሰራት |

## የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- የተነጣጠሉ ድምፆችን በማጣመር ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- የተጣመሩ ቃላትን በመነጣጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን በመነጠል ወይም በማጣመር እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በመነጠልና በማጣመር ከለዩ በኋላ ድምፆቹ በደንብ እንዲሰሙ

አድርገው እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡

- የተመረጡ ድምፆችን እየጠሩ እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በማጣመርና በመነጠል ሆሄያቱን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ባለሶስት ሆሄ ቃላትን በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ በካርቶን፣ .... ላይ በመፃፍ ይስጧቸው፤ ያሳዩዋቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውር ተማሪዎች ካሉ በቃል ያንብቡላቸውና ምላሻቸውን ይቀበሏቸው
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- ፊደላትን እያሳዩ (በጥቁር ሰሌዳ፣ በፊደል ካርድ፣ በባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣ ከመፅሐፋቸው) በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ድምፁን በተናጠል በመጥራት ከዛም ድምፆችን በማጣመር ባለሶስት ሆሄ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን የመነጠልና የማጣመር ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ታሳቢ ባደረገ መልኩ ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

| መርጃ መሳሪያዎች፡- | የማስተማሪያ ስልቶች፡- |
| --- | --- |
| - የቃላት ፋይል | - የግል ስራ |
| - ቅርፃ ቅርፅ | - በቡድን ማደራጀት |
| - የፊደል ካርድ | - በጥንድ ማሰራት |

## 🕮ንባብ

## መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ በመጀመሪያ እርስዎ ድምፅዎን ከፍ አድርገው በማንበብ አርዓያ ሆነው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በጣት እየጠቆሙ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በትዕዛዙ መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

የማስተማሪያ ስልት፡- ዘዴዎችን እንደሁኔታው እየቀያየሩ ይተግብሩ፡፡

- ማሚቶ ንባብ
- ህብረት ንባብ
- ትብብር ንባብ
- ጥንድ ንባብ
- ፅጥታ ንባብ

## ✍ ጽሕፈት

## ቅጥያዎችን መለየት

መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎችና ቃላትን በፊደል ካርድ ላይ በተናጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉ የተለመዱ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- ቅጥያዎችን በመነጠልና በማጣመር እየሰሩ ያሳዩዋቸው፡፡
- በቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በመነጠል እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- በተተኳሪ ፊደላት ሶስት ሶስት ፊደላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- በመፅሐፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

መርጃ መሳሪያ፡- - ቅጥያዎችን የያዘ ቅርፃ ቅርፅ ይጠቀሙ - ቻርት

- የፊደል ካርድ

## 👂 ማዳመጥ

መምህር፡-

❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
❖ ከርዕሱ ተነስተው ምንባቡ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
❖ ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
❖ የምንባቡን ዋና መልዕክት እንዲገልፁ እድል ይስጧቸው፡፡
❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ምንባቦችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

# ሲመክሩት ያልሰማ

አማን ፣ ሮማን ና ሃናን የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ምሳቸውን የሚበሉት በጋራ ነው። ሮማንና ሃናን የሳይንስ መምህራቸው ባስተማሯቸው መሠረት የግል ንፅናቸውን ይጠብቃሉ። አማን ግን ከምግብ በፊትና በኋላ እንኳ እጆቹን አይታጠብም። ሮማንና ሃናም ሁልጊዜ የግል ንፅህናህን ጠብቅ እያሉ ይመክሩታል። እሱ ግን አይሰማቸውም። አልፎ አልፎ ሆዴን አመመኝ ይላል። ጓደኞቹም የሚያምህ የግል ንፅህናህን ስለማትጠብቅ ነው። አማን ከትምህርት ቤት በተከታታይ ሦስት ቀን ቀረ።

*** አማን የቀረው ምን ሆኖ ይመስላችኋል? ***

ጓደኞቹም ምን ሆኖ ይሆን ብለው ሊጠይቁት ወደ ቤቱ ሄዱ። ቤት ሲደርሱ አማን በጣም ታሞ ተኝቷል። አይዞህ መድኃኒቱን በአግባቡ ተጠቀም። ቶሎ ይሻልሃል በማለት አፅናኑት። አማንም እናንተ የምትሉን ሰምቼ ቢሆን እንደዚህ አልሆንም ነበር አላቸው። መፀፀቱን ነገራቸው። ከምግብ በፊትና በኋላ እጆቹን መታጠብ ልምድ አድርጎ መተግበር ጀመረ።

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው።
- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው።
- ምንባቡ እየተነበበ እያለ ለተጠየቁት ጥያቄ የመለሱት መልስ (ግምታቸው) ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፤ ያረጋግጡ።
- ከተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው።
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው።

## ቃላት

## መምህር፡-

- በቃላት ውስጥ የተጓደሉትን ሆሄያት አሟልተው እንዲፅፉ ያድርጓቸው።
- ከተማሪ መፅሐፍ ከተሰጡት ምሳሌዎች በተጨማሪ ሌሎች ምሳሌዎችን ሰርተው ያሳዩዋቸው።
- ከተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው።

## 📖ንባብ

## መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ በመጀመሪያ እርስዎ አርዓያ በመሆን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሏቸው፤ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

## የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

መምህር፡-

- የተነጣጠሉና የተጣመሩ ድምፆችን በማጣመርና በመነጠል ሰርተው ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ድምፆችን ከቃላት ውስጥ በመነጠልና በማጣመር እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
- በቃል ውስጥ ያሉ ድምፆችን በጥንድ/ በቡድን በመነጠልና በማጣመር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን በመነጠል ወይም በማጣመር እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- የተመረጡ ድምፆችን እየጠሩ እንዲያጣምሩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች መፅሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ፊደሎች እያጣመሩና እየነጠሉ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡
- በመማሪያ መፅሐፋቸው ውስጥ የቀረቡትን የመነጠልና የማጣመር ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል መስራታቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡
- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ታሳቢ ባደረገ መልኩ ትምህርቱን ያቅርቡላቸው፡፡
- ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

## ✍ጽሕፈት

## መምህር፡-

- ✓ በቃል ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን በመደጋገም አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ ያስደርጉ፡፡
- ✓ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሠረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተመሳሳይ ስራዎችን እንዲሰሩ ይስጧቸው፡፡
- ✓ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡
- ✓ ተከታታይ የሆነ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

## 📖ንባብ

### መምህር

- በመፅሐፋቸው ላይ ያለውን በተተኳሪ ፊደላት የተመሰረተውን አረፍተ ነገር በመጀመሪያ እርስዎ አርዓያ በመሆን የድምፅዎን ቅላፄ በመለዋወጥ በማንበብ ያሳዩዋቸው፡፡
- ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ደጋግመው እንዲያነቡ እድል ይስጧቸው፡፡
- በትክክል ማንበባቸውን እየተዘዋወሩ ያዳምጧቸው፡፡
- ማበረታቻ ቃል ይጠቀሙ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዋናውን ተተኳሪ ርዕስ መነሻ በማድረግ የወጡ ሁለት የተለያዩ የአዳምጦ መናገር ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡትን የምንባቡን ርዕሶችም ከስዕሎች ጋር በማዛመድ የራሳቸውን ግምት እንዲናገሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዳመጡትን ምንባብ ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ የተደረገ ሲሆን ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡

በሀሳብ ካርታ ላይ በጅምር(የተጓደሉ) ሀሳቦችን በማስፈር የቃላት እውቀታቸውን አዳብረዋል፡፡ በቃላት ውስጥ የመጀመሪያና የመጨረሻ ድምፆችን ለይተው ማሳየት ችለዋል፡፡ እንዲሁም በመነጣጠልና በማጣመር የለዩዋቸውን ቃላት በማንበብ እና በመፃፍ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ በቃላት ውስጥ የተጓደሉ ፊደላትን በማሟላት ቃላት መመስረት ተለማምደዋል፡፡ በጽሑፍ ውስጥ ተተኳሪ ፊደሎች ያሉባቸውን አጫጭር አረፍተ ነገሮች አንብበዋል፡፡ በተጨማሪም በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቅጥያዎችን በመነጠል ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በቃላት ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን በመደጋገም አዳዲስ ቃላትን መስርተዋል፡፡

በተማሪ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ይዘቶች ተግባራዊ በማድረግ የራስዎን መመዘኛ መንገድ እና የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የክህሎት እድገት ይፈትሹ፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ያድርጉላቸው፡፡

18
ክፍለ ጊዜ

# ምዕራፍ አስር
# የቤት እንስሳት

**የምዕራፉ አላማዎች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ያዳመጡትን ጽሑፍ ዋና ሃሳብ ከተጨባጩ አለም ጋር ያዛምዳሉ፤
- አዳዲስ ቃላትን ከፍ ባለ ድምፅ ይጠራሉ፤
- ባለሶስት ፊደል ቃላትን በማጣመርና በመነጠል ያነባሉ፤
- በአዳዲስ ሆሄያት የተመሰረቱ ቃላትን ያነባሉ፤
- ቅጥያዎችን ይነጣጥላሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- አዳምጦ መናገር
- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምፅ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት
- ማፍለቅና መረዳት
- ማንበብ
- መፃፍ
- ድምፀት

## ማዳመጥ

መምህር፡-

- ❖ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎች ያስተዋውቁ፡፡
- ❖ ከርዕሱ ተነስተው ምንባቡ ስለምን ሊያወራ እንደሚችል የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግምታቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ርዕሱን እና ስዕሉን በማየት የሚያዳምጡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተናጠል ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በአካባቢያቸው የሚገኙ የቤት እንስሳት ስሞችን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ትኩረታቸው ከርስዎ ጋር መሆኑን ለማረጋገጥ ምንባቡን በመሃል ቆም በማድረግ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ምላሻቸውን እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፡፡
- ❖ (ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ምንባቦችን በማምጣትና የራስዎን ታሪክ ፈጥረው ለተማሪዎች ያንብቡላቸው)

## ታማኙ ውሻ

ውሻ የሰው ልጅን በቅንነትና በታማኝነት የሚያገለግል የቤት እንስሳ ነው፡፡ ውሻ የመጀመሪያው ለማዳ የቤት እንስሳ ነው፡፡ ውሻ የጌታውን እና በተደጋጋሚ ያየውን ሰው ጠረን የሚያውቅበት ልዩ ተፈጥሮአዊ ችሎታ አለው፡፡ ይህ እንስሳ ጅራቱን በማወዛወዝ ለጌታው/ለባለቤቱ/ ፍቅሩን ይገልፃል፡፡ ውሻ በእክብካቤ ከተያዘ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ጌታውን /ባለቤቱን በታማኝነት ያገለግላል፡፡የጥበቃነት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

*** ውሻ ለሰው ልጅ ምን ምን ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣል?***

ውሻ ስልጠና ካገኘ ወንጀለኛን አነፍንፎ የማግኘት ብቃት አለው፡፡ በተጨማሪም ቤት ውስጥ ልጆችን በማጫወት ፣ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ሰርከስ በመስራት ሰዎችን ያዝናናል፡፡ ይሁን እንጂ ውሾች በእንክብካቤና በፅዳት ካልተያዙ በሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ስለዚህ ንፅህናውን የጠበቀ ምግብ መስጠት፣ በንፅህና መያዝና በባለሙያ ማስከተብ አለብን፡፡

(ምንጭ፡-ታለጌታ ይመር፡፡(2010)፡፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማርያ አጋዥ መፅሀፍ፤ ከ 1ኛ-4ኛ ክፍል ፣ ገፅ 87-88 የተወሰደ)

## አዳምጦ መናገር

መምህር፡-

- ርዕሱ ሲነገራቸውና ስዕሉን አይተው የገመቱትን እንዲያስታዉሱ ያድርጓቸው፡፡
- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ርዕሱንና ስዕሉን መሰረት አድርገው ባዳመጡት መሰረት ግምታቸው ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፡፡
- ምንባቡ እየተነበበ እያለ ለተጠየቁት ጥያቄ የመለሱት መልስ (ግምታቸው) ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቋቸው፤ ያረጋግጡ፡፡
- ከተማሪ መፅሐፍ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ምላሻቸውን በተናጠል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ትዕዛዝ፡- የሚከተሉትን የቤት እንስሳት ስሞች ለምግብነት
የሚያገለግሉና ለጭነት የሚያገለግሉ በማለት
ለይታችሁ ጻፉ።

ግመል | በግ | ላም | አህያ | በቅሎ
ዶሮ | ፈረስ | ፍየል | በሬ

**የቤት እንስሳት**

| ለምግብነት የሚያገለግሉ | ለጭነት/ለመጓጓዣነት |
|---|---|
| • በግ<br>• ዶሮ<br>• ላም<br>• ፍየል<br>• በሬ<br>• ግመል | • ፈረስ<br>• አህያ<br>• በቅሎ<br>• ግመል |

*መምህር፡-*

- መጽሐፍላይ የቀረበውን የቤት እንስሳ ቻርት በደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጓቸው።

-ተማሪዎችቤት እንስሳት ስሞችን በየምድባቸው እየለዩ እንዲያስቀምጡ ያድርጓቸው።

## ⊶ የቃላት ጥናት

